የያዕቆብ መልእክት

ትምህርት ሁለት

ሁለቱ የጥበብ መንገዶች

ተርጓሚ፡ እሸቴ በለጠ

THIRD MILLENNIUM MINISTRIES

Biblical Education. For the World. For Free.

© 2015 by Third Millennium Ministries

All rights reserved. No part of this publication may be reproduced in any form or by any means for profit, except in brief quotations for the purposes of review, comment, or scholarship, without written permission from the publisher, Third Millennium Ministries, Inc., 316 Live Oaks Blvd, Casselberry, Florida 32707.

እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ **መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ** የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡ ሥርዓተ-ትምህርታችን በአሁኑ ወቅት ከ192 በላይ በሆኑ አገሮች ውስጥ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ጎብኙ፡፡

ማውጫ

1. **መግቢያ**

2. **መመሪያ ሰጭ ጥበብ**
   ሀ. ፍላጎት
      1. ሞጋች ፈተናዎች
      2. የተለያዩ ፈተናዎች
   ለ. መመሪያ
      1. መፈተን
      2. ጽናት
      3. ብስለት
      4. ብድራት
   ሐ. እምነት

3. **ተግባራዊ ጥበብ**
   ሀ. ፍላጎት
      1. ምድራዊ ጥበብ
      2. ሰማያዊ ጥበብ
   ለ. መመሪያ
      1. የእግዚአብሔር ህግ ስነ-ልክ
      2. የእግዚአብሔር ህግ ቅድሚያዎች
   ሐ. እምነት
      1. እምነትና ሥራ
      2. እምነትና መጽደቅ

4. **ማጠቃለያ**

መግቢያ

ሁላችንም በአንድም ሆነ በሌላ ጊዜ ግራ የሚያጋቡና ተስፋ የሚያስቆርጡ ፈታኝ ሁኔታዎች ይገጥሙናል፡፡ እንግዲህ በእንደነዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ ስናልፍ ምን እየተከናወነ እንደሆነ በትክክል የተገነዘበና ልንከተለው የሚገባንን ጥቂት ተግባራዊ ምክሮችን ሊለግሰን የሚችል ጓደኛ ማግኘት በእጅጉ እንናፍቃለን፡፡ ይህ ዓይነቱ ጓደኛ ትልቅ ደስታን ሊያስገኝልን የምንችልበት ጥበብ ምንጭ ሊሆንልን ይችላል፡፡

በበርካታ መንገዶች፣ የአዲስ ኪዳን መልእክት የሆነውን የያዕቆብን መልእክት በመጀመሪያ በተቀበሉት ቀደምት ክርስቲያኖችም ዘንድ ጉዳዩ እንዲሁ ነው፡፡ አብዛኞቹን ግራ ያጋቡና ተስፋ ያስቆረጡ ፈታኝ ሁኔታዎች እየገጠሟው በእነርሱ ውስጥ አልፈዋል፡፡ ያዕቆብም ጥበብን ሊያጋራቸው ጽፎላቸዋል፡፡ በእነርሱ ሁኔታዎች ውሰጥ የእግዚአብሔርን በጎ ዓላማዎች ሊያሳስባቸው አስቦ ጽፎላቸዋል፡፡ ሊከተሉት የሚገባውን አስተማማኝ መመሪያ እግዚአብሔር እንደሰጣቸው እንዲያውቁ ያደርጋል፡፡ የእግዚአብሔርን ጥበብ የራሳቸው ቢያደርጉ፣ ታልቅ ደስታን እንደሚጎናጸፉ ትልቅ ማረጋገጫን ይሰጣቸዋል፡፡

የያዕቆብ መልእክት ከተሰኘው ተከታታይ ትምህርታችን ይህኛው ሁለተኛው ትምህርታችን ሲሆን፣ ከያዕቆብ መልእክት ተያያዥ መሪ ሃሳቦች መካከል በእንዱ ላይ ያተኩራል፡፡ ይህንን ትምህርታችንን "ሁለቱ የጥበብ መንገዶች" የሚል ርዕስ የሰጠነው ሲሆን፣ ለዚህም ምክንያቱ እግዚአብሔር ለመጀመሪያዩቱ ቤተክርስቲያን የሰጣቸውን ሁለቱን ዓይነት ጥበቦች ይህ መጽሐፍ እንዴት እንደገለጻቸው ማብራሪያ ስለምንሰጥበት ነው፡፡ ደግሞም፣ ዛሬ እኛ እንደ ክርስቶስ ተከታዮች ልንከተላቸው የሚገቡንን ተመሳሳይ አቅጣጫዎች እንዴት እንደሚሰጠን እንመለከታለን፡፡

ቀደም ባለው ትምህርታችን፣ የያዕቆብን መልእክት አወቃቀርና ይዘት በተመለከትንበት ወቅት እንዳየነው መልእክቱ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበረውን እውቅ የአይሁድ ጥበባዊ ስነ-ጽሑፍ እንደሚያንጸባርቅ ገልጸናል፡፡ የመልእክቱን ቀደምት ዓላማም በዚህ መንገድ ጠቅለል አድርገን አስቀምጠናል፡

> **በመከራዎቻቸው ውስጥ ደስታን ያገኙ ዘንድ ጥበብን ከእግዚአብሔር ዘንድ አጥብቀው እንዲፈልጉ የዕቆብ ለተደራሲያኑ ጥሪ ያስተላልፋል፡፡**

ያዕቆብ የተጠቀመባቸው ቃላት "ጥበብ" የሚለው ቃል - በግሪኩ *sophia* (σοφία) የሚለው እና "ጠቢብ" የተሰኘው ቃል በግሪኩ *sophos* (σοφός) በደብዳቤው ውስጥ አገልግሎት ላይ ያዋላቸው በሁለት ክፍሎች ውስጥ ብቻ ነው፡፡ እነዚህን ቃላት የምናገኛቸው በ1፡2-18 እና በድጋሚ ደግሞ በ3፡13-18 ውስጥ ነው፡፡ እነዚህ ምንባቦች ለየብቻቸው እጅግ ወሳኝ ናቸው ምክንያቱም እያንዳንዳቸው ያዕቆብ እንድንከተላቸው ጥሪ የሚያቀርብባቸውን ሁለት የጥበብ መንገዶች ስለሚያጣቅሱ ነው፡፡

እንግዲህ፣ አንዳንድ ሰዎች በያዕቆብ መጽሐፍ ውስጥ ስለተገለጠው ጥበብ በሚስቡበት ወቅት፣ ያዕቆብ በምድራዊና በሰማያዊ ጥበብ መካከል ስላስቀመጠው ልዩነት እንደሚያስቡ መግለጽ ይገባናል፡፡ በዚህ ትምህርት ወደ ኋላ ላይ እነዚህን ሁለቱንም ጥበቦች እንመረምራለን፡፡ ለአሁኑ ዓላማችን ግን፣ በአይሁዳውያን የጥበብ ትውፊት ውስጥ ተለይተው በሚታወቁት በሁለቱ ዋና የጥበብ መንገዶች ላይ ትኩረት እናደርጋለን፡፡ የመጀመሪያው "ማሳሰቢያ ሰጪ ጥበብ" ብለን የጠራነው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ "ተግባራዊ ጥበብ" ብለን የምንጠራው ነው፡፡

ማሳሰቢያ ሰጭ ጥበብ በግልጽ የተንጸባረቀው እንደ ኢዮብና መክብብ በተሰኙ መጻሕፍት ውስጥ ነው፡፡ እነዚህ መጻሕፍት ከፈተናና ከችግሮች በስተጀርባ ያለውን የእግዚአብሔርን ዓላማ የሚጠቁሙ አመለካከቶችን ያስሳሉ፡፡ ተግባራዊ ጥበብ በሌላ ጎኑ ደግሞ፣ በገሃድና በግልፅ ተቀምጦ የሚገኘው በምሳሌ መጽሐፍ ውስጥ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ በተቀዳሚነት የሚያገለግለው በዕለት ከዕለት ሕይወታችን ምክርና መመሪያ ለመስጠት ነው፡፡

በያዕቆብ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙትን ሁለቱን የጥበብ መንገዶች ስንመረምር፣ በመጀመሪያ የማሳሰቢያ ሰጪ ጥበብን መንገዶች እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ የተግባራዊ ጥበብን መንገዶ እንመለከታለን፡፡ እስኪ አስቀድመን በማሳሰቢያ ሰጪ ጥበብ ላይ ያዕቆብ የሰጠውን ትኩረት እንመለከት፡፡

ማሳሰቢያ ሰጪ ጥበብ

ሁላችንም ተረድተነዋል ብለን እርግጠኛ ከነበርንባቸውና ኋላ ግን ራሳችንን ተሳስተን ከምናገኝባቸው ሁኔታዎች ጋር ስንጋፈጥ ራሳችንን እናገኘዋለን፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ከተገለጸው ነገር ባሻገር ያለውን ነገር ለሁለተኛ ጊዜ በበለጠ ጥንቃቄ መመልከትና በእውነት ምን እየሆነ እንዳለ ለማስተዋል እንገደዳለን፡፡ በበርካታ መንገዶች፣ ያዕቆብ የመጽሐፉን ዋና አካል የጀመረው በዚህ ሁኔታ ነው፡፡ ተስፋ አስቆራጭ ከሆኑትና ከተገለጡት ሁኔታዎቻቸው አሻግረው እንዲመለከቱና በሕይወታቸው በእውን ምን እየተከናወነ እንደሆነ የሚያስተውሉበትን መረዳት እንዲጨብጡ ያዕቆብ ለተደራሲያኑ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

ያዕቆብ ይህንን ዓይነቱን ማሳሰቢያ ሰጪ ጥበብ እንዴት እንደዳሰሰው በሦስት መንገዶች እንመለከታለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የተደራሲያኑን ፍላጎት እንዳስሳለን፡፡ ሁለተኛ፣ ያዕቆብ የሚሰጣቸውን መመሪያ እንመለከታለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ በማሳሰቢያ ሰጪ ጥበብና በእምነት መካከል ስላለው ግንኙነት እንቃኛለን፡፡ አስቀድመን የያዕቆብ ተደራሲያን ማሳሰቢያ ሰጪ ጥበብ የሚያስፈልጋቸው ስለ መሆኑ እንመለከታለን፡፡

ፍላጎት

ቀደም ባለው ትምህርታችን፣ የዚህ ደብዳቤ ቀደምት ተደራሲያን በተቀዳሚነት የመጀመሪያዎቹ አይሁዳዊ ክርስቲያኖችን ያካተተ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ የእስጢፋኖስን መሰዋት ተከትሎ በመጣው የመከራ ማዕበል ምክንያት ከኢየሩሳሌም ተባርረው የወጡ ይመስላል፡፡ ያዕቆብ ከጻፈው ሃሳብ በግልጽ እንደምንረዳው እነዚህ ሰዎች በየተበተኑባቸው ሃገሮች ከገጠሙዋቸው ተስፋ አስቆራጭ እና ግራ አጋቢ ሁኔታዎች የተነሳ እገዛ የሚያስፈልጋቸው በርካታ ሰዎች ናቸው፡፡

በያዕቆብ 1፡2 ውስጥ እንደምናስተውለው ያዕቆብ በእነዚህ ፍላጎቶች እንደተሞላ ነው፡፡ ያዕቆብ የመልእክቱን የመክፈቻ ጥቅስ አስከትሎ ወዲያውኑ ያነሳው እንዲህ የሚል ነው፡

> **ወንድሞቼ ሆይ፥ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፥ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት (ያዕቆብ 1፡2)**

የያዕቆብን ተደራሲያን ፍላጎት ለመረዳት፣ የዚህን ምንባብ ሁለት ገጽታዎች መመልከት በጣም ይጠቅማል፡፡ በመጀመሪያ፣ ሞጋች ፈተናዎችን እንመረምራለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ የያዕቆብ ተደራሲያን የገጠሟቸውን የተለያዩ ዓይነት ፈተናዎች መርምረን እንደርስባቸዋለን፡፡ እስኪ አስቀድመን ሞጋች ፈተናዎችን እንመልከት፡፡

ሞጋች ፈተናዎች

በያዕቆብ 1፤2 ውስጥ የሚገኘውና "ፈተና " ተብሎ የተተረጎመው ቃል በግሪኩ *peirasmos* (πειρασμός) የተሰኘው ስም ነው፡፡ ይኸው ቃል "ፈተና" "መከራ" እና "ምርመራ" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ፣ ግሳዊ ቅርፁ "መፈተን" "በመከራ ውስጥ ማለፍ" እና "መመርመር" የሚል ትርጉም ይኖረዋል፡፡ የዚህን ትርጓሜ መጠነ ልክ በትክክል መገንዘብ የመልእክቱ ተደራሲያን እተጋፈጡ ያለውን ሁኔታ እንድንጨብጥ ያስችለናል፡፡ በውጤቱም፣ የተለያዩ ፈተናዎች ይገጥማቸዋል፣ እነዚህም ፈተናዎች መከራ ያመጡባቸዋል ያም መንገዳቸውን እጅግ የሚፈታተን ይሆናል፡፡

እንደ አለመታደል ሆኖ ግን፣ አብዛኛውን ጊዜ የዘመናችን ክርስቲያኖ ፈተናዎች፣ መከራዎችና የተለያዩ ፈታኝ ሁኔታዎች በያዕቆብ ልቡና ውስጥ እንዳለው ዓይነት እርስ በርስ የተያያዙ መሆናቸውን ከመረዳት ይልቅ የተለያዩ እንደሆኑ እናስባለን፡፡ ነገር ግን እንደ ኢዮብ መጽሐፍ ያሉት የጥበብ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚሳዩን፣ እነዚህ ጽንሰ-ሃሳቦች የእግዚአብሔርን ህዝብ የሚፈታተኑ የተለያዩ መከራዎችን ልዩ ልዩ ገጽታ አመልካቾች ናቸው፡፡

ሞጋች ሁኔታዎች፣ ፈተናዎች ናቸው ምክንያም ጽናትን የሚጠይቁ አስቸጋሪ ሁኔታዎች መሆናቸው ነው፡፡ ሆኖም እነዚህ ሁኔታዎች ከግብረ-ገብ ነክ ገዳዮች የጸዱ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ እነዚህም ፈተናዎች በተሳሰተ ወይም ከኃጢአት ጋር ተያያዥነት ባላቸው መንገዶች ምላሽ እንድንሰጥ ይፈታተኑናል፡፡ ደግሞም ሞጋች ሁኔታዎች እግዚአብሔር እኛን የሚፈትሽባቸው

መንገዶችም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እግዚአብሔር የልባችንን ሁኔታ የሚመረምርባቸውና ንጽህናቸውን የሚፈትሽባቸውም መንገዶች ናቸው፡፡

ሞጋች ከሆኑ ፈተናዎች የሚመነጨውን ፍላጎት በልቡናችን ከያዝን በኋላ፣ ያዕቆብ በ1፡2 ውስጥ የጠቀሳቸውን በርካታ ዓይነት ፈተናዎች ወደመመልከቱ እንሸጋገራለን፡፡

በርካታ የፈተና ዓይነቶች

ያዕቆብ ስለ በርካታ ዓይነት ፈተናዎች በሚናገርበት ወቅት፣ በመጀመሪያዩቱ ቤተክርስቲያን ውስጥ በነበሩ ባለጠጋ አማኞችና በድሆች መካከል የነበሩ ግጭቶችንና የተለያዩ አከራካሪ ጉዳዮችን በእነርሱም ምክንያት የተከሰቱ ችግሮችን አመልክቷል፡፡

በአንድ በኩል፣ ድሃ አማኞች ገጥመዋቸው ስለነበሩ ተግዳሮቶች ያዕቆብ በስፋት ጽፏል፡፡ የሐዋርያት ሥራ 2-6 እንደምናስተውለው፣ በኢየሩሳሌም በምንተገነው የመጀመሪያዩቱ ቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙ ድሆች ነበሩ፡፡ ያዕቆብ የጻፈው በመከራ ምክንያት ከኢየሩሳሌም ለተበተኑ አማኞች እንደመሆኑ መጠን፣ ምናልባትም የድሆቹ ቁር በርክቶ ሊሆን ይችላል፡፡

በ1፡9 እና በ4፡6 ውስጥ፣ ያዕቆብ እነዚህን አማኞች "ትኑት" ወይም በግሪኩ *tapeinos* (ταπεινός) በማለት ይጠራቸዋል፡፡ የዚህ ቃል ትርጓሜው "በማኅበረሰቡ ውስጥ ዝቅተኛ ስፍራ ያላቸው" ማለት ነው፡፡ በ2፡2፣3፣5 እና 6 ውስጥም "ድሆች" ወይም በግሪኩ *ptochos* (πτωχός) ብሎም ይጠራቸዋል፡፡ ትርጓሜውም "ዝቅተኛ ኤኮኖሚ ያላቸው" ማለት ነው፡፡ በ1፡27 ውስጥ ደግሞ፣ "ወላጅ ከሌላቸውና ከመበለቶች" ጋር ያጣቅሰዋል፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍትም ይህንን ቡድን ለድህነትና ለጉስቁልና በማኅበረሰቡም ዘንድ ለመገፋት የተጋለጡ እንደሆኑ ያመለክታሉ፡፡ በ2፡2 ውስጥ እነዚህ ድሃ አማኞች "ያረጁና የተቦጫጨቁ ልብሶችን" ይለብሱ እንደነበር ያዕቆብ ያመለክታል፡፡ እንደ 2፡15 አገላለጽ፣ አንዳንዶቹ እንዲያውም እጅግ በጣም ድሆች ከመሆናቸው የተነሳ "የዕለት ጉርስና ልብስ" እንኳን እንዳልነበራቸው እንገነዘባለን፡፡

> **ያዕቆብ ለድሆች ጉዳይ ከፍተኛ አጽንዖት ሰጥቷል፡፡ ያዕቆብ ሊነግረን እየሞከረ ያለውን ጉዳይ በመንፈስ ድሆች ስለሆኑ ሰዎች ነው ብለን ለመገመት እንሞክራለን፡፡ አዎን በእርግጠኝነት ትኑታን ልንሆን እንደሚገባን፣ በመንፈስ ድሆች ልንሆን እንደሚገባን ተናግሯል፡፡ ሆኖም ደግሞ በአካላዊ (በቁሳዊ) ሁኔታቸው ድሆች ስለሆኑ ሰዎች ጉዳይም በትክክል ተናግሯል፡፡ ሉቃስ ስለ ብጽእና ኢየሱስ ያስተማረውን እንደዘገበልን ዓይነት "ድሆች ብጹዓን ናቸው፡፡" እናም ያዕቆብ ቢያን ስ ማለት የፈለገው ስለ አካላዊ ወይም ቁሳዊ ድሆች ጉዳይ መሆኑ እሙን ነው፡፡**
>
> **እህ፣ ለምን እነርሱ ለብቻቸው ብጹዓን ተባሉ? ብንል ምላሹ የሚሆነው፣ የመንግሥቱ የአሠራር መንገድ እንደዚያ ስለሆነ ነው፡፡ የመንግሥቱ ዋና ጉዳይ ደካሞችን ከፍ ማድረግ ብርቱዎችን ደግሞ ትኑታን ማድረግ ነው፡፡ ያንንም በዚህ ዘመን ሕይወት ማድረግ ይቻላል፡፡ ባለጠጋ ከሆናችሁ፣ ብርቱዎች ከሆናችሁ እና ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ከሆናችሁ ራሳችሁን ትኑታን ማድረግ ትችላላችሁ፡፡ ድህነትን በመንፈስ ድሃ ከመሆን ጋር ሲያያይዘው ያዕቆብ ግቡ ያደረገው፣ የትኑትናን ጉዳይ ሊያሰምርበትና ሊያዳብረው ፈልጎ ነው፡፡ ሆኖም ግን በእውን በአካል ወይም በቁሳዊ ረገድ ድሆች ስለሆኑም የሚያወሳው ብዙ ነገር አለው፡፡ ያም ሃብታቸው በሰማይ እንደሆነ፣ መንግሥታቸው ሰማያዊ እንደሆነ፣ ብድራታቸውም ሰማያዊ እንደሆነና ሃብታቸውም በባህርዩ ሰማያዊ እንደሆነ ያረጋግጣል፡፡ እናም፣ ስለዚህ ወደፊት የሚመጣው ነገረ-ፍፃሜ ሁሉን ነገር ይቀለብሳል ማለት ነው፡፡ በዚያን ጊዜ ደካሞች ብርቱ ይሆናሉ፡፡ ማለትም እግዚአብሔር ቅሬታዎችን ይሰበስባል፣ ህሙማንን ይሰበስባል፣ ድሆችን ይሰበስባል፣ በመንግሥቱም ውስጥ ከፍ ከፍ ያደርጋቸዋል፡፡ በዚያም የትዕቢተኞችን ኩራት ያወርዳል ትኑትም ያደርጋቸዋል፡፡**
>
> - **ዶ/ር ቶማስ ኤል. ኬን**

በቤተክርስቲያን ውስጥ ትኑታንና ድሆች የሚደርሱባቸውን በርካታ ተግዳሮቶች ያዕቆብ ጠቃቅሷል፡፡ ጥቂቱን ብንጠቅስ፣ በ1፡9 ውስጥ፣ አንዳንዶቹ ራሳቸውን ከደዋል፡፡ ምን ለማለት ነው፣ በእግዚአብሔር ለዘላለማዊ ድነት እንደተጠሩ ህዝቦች፣ "ባላቸው የሥልጣን እርከን መመካትን" እምቢ ብለዋል፡፡ እንደ 3፡9 አገላለጽ ደግሞ፣ ያሉበት ሁኔታ እግዚአብሔርን በሚያከብሩበት አንደበታቸው፣ ሌሎችን ሰዎች እንዲራገሙ ተፈታትኗቸዋል፡፡ በ3፡14 ደግሞ፣ በሌሎች ላይ "መራርነት ያለበት ቅናት" እንዲነግሥባቸውና "በራሳቸው የመመካት" ፈተና ውስጥ እየገቡ ያሉትን አስጠንቅቋል፡፡ በ4፡1 እንደምናገኘው፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ በሚፈጠር "ጦርነትና ጠብ" ውስጥ የመዘፈቅ ፈተና እንደከበባቸው ተናግሯል፡፡

ደግሞም በ5፡7 ውስጥ የጌታን መመለስ በትዕግሥት በመጠባበቅ ትዕግሥትን አልባነትን እንዲያስወግዱ ያዕቆብ ለድሆች ጥሪውን አቅርቧል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ባለጠጋ አማኞችም ተግዳሮት ገጥሟቸዋል፡፡ የሐዋርያት ሥራ 2-6 እንደሚነግረን፣ በመጀመሪያዩቱ ቤተክርስቲያን ውስጥ የነበሩ ሃብታሞች ቢያንስ ጥቂቶቹ፣ በክርስቶስ ሆነው ድሆች የሆኑ ወንድሞቻቸውንና እህቶቻቸውን ችግር መካፈል ግድ ሆኖባቸው ነበር፡፡ ምንም እንኳ በመከራ ምክንያት በየስፍራው ቢበተኑም፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ ጥሩ የሀብት ቁመና የነበራቸው በርካታ ሰዎች ነበሩ፡፡

ያዕቆብም እነዚህን ባለጠጋ አማኞች በበርካታ መንገዶች ገልጧቸዋል፡፡ በ1፡10፤ በ2፡6 እና በ5፡1 ውስጥ፣ "ባለጠጎች" ወይም ብግሪኩ *plousios* (πλούσιος) በማለት በቀላሉ አስቀምጧቸዋል፡፡ ይህም አገላለጽ በዘመኑ በማኅበረሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ ለሚሰጣቸው ሰዎች አገልግሎት ላይ የሚውል የተለመደ አባባል ነበር፡፡ እንደ 2፡6 አገላለጽ፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ የነበራቸው ስፍራ ከፍተኛ ስለነበር ሌሎችን ሰዎች አዘውትረው ወደ ሸንጎ ያቀርቡ ነበር፡፡ ምዕራፍ 4፡13 እንደሚነግረን፣ ገንዘብን ለማግኘት ሲሉ በርካታ የንግድ ጉዞዎችን ያደርጉ ነበር፡፡ ምዕራፍ 5፡2-3 እንደሚጠቁመን፣ በነበሯቸው ልብሶች ብሮችና ወርቆችም ይመኩ ነበር፡፡ ደግሞም በ5፡5 ውስጥ፣ ቢያንስ ጥቂቶቹ "የቅምጥልነትና የሴሰኝነት" ኑሮ ይኖሩ እንደነበር ተጠቅሷል፡፡

ብልጥግና የራሱ ፈተናዎች እንዳሉበት ያዕቆብ ያውቃል፡፡ እንደ 1፡10 አገላለጽ፣ ከኃጢአታቸው ንስሓ እንደገቡ ሰዎች የነበራቸውን ትኑት ስብዕና በመዘንጋት በራሳቸው ወደ መመካት ፈተና ውስጥ ገብተው ነበር፡፡ ምዕራፍ 1፡27 እንደሚነግረን፣ ብልጥግናቸው "በዓለም እርኩሰት" ውስጥ እንዲወድቁ ተፈታትኗቸዋል፡፡ በ2፡7 ደግሞ፣ በሸንጎ ፊት የሃሰት ምስክር በመሆን በስህተት አሠራር ተፈትነዋል፡፡ በ2፡16 ደግሞ፣ ድሆችን አስመልክቶ ደንታ ቢስ ወደመሆን እንዳዘነበሉ ያዕቆብ ይናገራል፡፡ እንደ 3፡9 አገላለጽ፣ እግዚአብሔርን እናከብራለን እያሉ፣ ከድሆቹ መካከል አንዳንዶቹን ሰዎች ይራገሙ ነበር፡፡ በ3፡14 ውስጥ ደግሞ፣ "መራርነት በሞላበት ቅናት" እና "በራስ ትምክህት" ውስጥ ተዘፍቀው እንደነበር እንገነዘባለን፡፡ በ4፡1 ደግሞ፣ በጦርነትና በጠብ ውስጥ ገብተዉ ነበር፡፡ ምዕራፍ 4፡13-16 እንደሚነግረን ደግሞ፣ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ምንም የማይመለከተው የሚመስል ዓይነት ሕይወት ይመሩ እንደነበር እናስተውላለን፡፡ 5፡3 ደግሞ ሀብትን ያለ ልክ እንዳከማቹ ይነግረናል፡፡

በያዕቆብ ተደራሲያን ውስጥ የነበሩ ባለጠጎችም ሆኑ ድሆች በርካታ ተግዳሮቶች እንደነበሩባቸው በግልጽ እንመለከታለን፡፡ ሁለቱም ቢሆኑ ያዕቆብ በመልእክቱ ያስተላለፈላቸው ጥበብ ያስፈልጋቸው ነበር፡፡

ተደራሲያኖቹ የሚያልፉባቸው የነበሩ ተግዳሮቶች ከፈጠሩባቸው ፍላጎቶች የተነሳ ማሳሰቢያዊ ጥበብ ሊቸራቸው እንደሚገባ በማሰብ በማሳሰቢያዊ ጥበብ ላይ ያዕቆብ የሰጠውን ትኩረት ቃኝተናል፡፡ አሁን ደግሞ፣ ወደ ሁለተኛው ጉዳይ መሸጋገር ይገባናል፡ ያም ለእነዚህ ፈተናዎች ያዕቆብ እንዴት መመሪያ እንደሰጠ የምናይበት ነው፡፡

መመሪያ

እንደ ክርስቶስ ተከታዮች ዕለት በዕለት በምናልፍባቸው ልምምዶች ውስጥ የክርስቲያናዊ ነገረ-መለኮትን በርካታ ገጽታዎች በቀላሉ እንረዳለን፡፡ ሆኖም ደግሞ ቀላል ያልሆኑ ሎሎች ክርስቲያናዊ ትምህርቶችም አሉ፡፡ ከልምምዳችን በስተጀርባ ያለውን የእግዚአብሔርን ስውር ዓላማ በትክክልና በጥልቀት ለመረዳት በእውነት የምንሻ ከሆነ፣ መመሪያ ማግኘት የግድ ያስፈልገናል፡፡ ማሳሰቢያ ጥበቦችን ማግኘት የምንችልባቸውን ውስጥን ዘልቀው የሚገቡ ምክሮችን ያዕቆብ ለግሶናል፡፡ እነዚያም በሕይወታችን ከሚገጥሙን ፈተናዎችና ተግዳሮቶች በስተጀርባ የሚገኘውን የእግዚአብሔርን ዓላማ የምናስተውልበትን አቅም አጎናጽፈውናል፡፡ ያዕቆብ በ1፡3-4 ውስጥ ተደራሲኑ እንዲጨብጡለት የሚፈልገውን ግንዛቤ እንዴት እንዳስቀመጠው እንመልከት፡

> **የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፤ … ትዕግሥትም ምንም የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም (ያዕቆብ 1፡3-4)።**

ያዕቆብ በዚህ ምንባብ ውስጥ የሰጠውን መመሪያ መመልከት የምንችልባቸው በርካታ መንገዶች ቢኖሩም፣ ልናነሳ ከምናስበው ጉዳይ አንፃር ግን አራቱን ብቻ እንመልከት፡፡ በመጀመሪያ፣ ያሉባቸው ፈታኝ ሁኔታዎች እምነታቸውን እየተፈታተነ እንደሆነ ያዕቆብ ይናገራል፡፡

መፈተን

ተደራሲያኑ እየገጠማቸው ያለውን ተግዳሮት ሲገልጸው "የእምነታችሁ መፈተን" የሚል ቃል ይጠቀማል፣ ይህም በግሪኩ *dokimion* (δοκίμιον) የተሰኘውን አባባል የሚይዝ ነው፡፡ ትርጓሜውም "ፍተሻ/ምርመራ" እንደማለት ሲሆን፣ ይህም የአንድን ነገር እውነተኝነት ለማረጋገጥ የሚደረገውን ምርመራ የሚያመለክት ነው፡፡ በዚህ ረገድ፣ ያዕቆብ እየተናገረ ያለው የእምነታቸውን እውነተኝነት ማረጋገጫ በሚል ዓይነት ነው፡፡

በውጤቱም፣ ተደራሲያኑ እያለፉባቸው ባሉ በርካታ ፈተናዎች ውስጥ እግዚአብሔር ያለው ዓላማ፣ የልባቸውን እውነተኛ ሁኔታ መመርመር እንደሆነ ያዕቆብ በደንብ ያብራራል፡፡ "መፈተናቸው" የእምነታቸውን እውነተኛ መሆን ያለመሆን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ እግዚአብሔር ስለፈተናዎች ያለው ዓላማ ይህ ነው የሚለው አመለካከት ለያዕቆብ አዲስ ነገር አይደለም፡፡ በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳናት ውስጥ በርካታ ጊዜ የተገለጠ ጉዳይ ነው፡፡ ለምሳሌ በዘዳግም 8፡2 ውስጥ፣ ሙሴ ለህዝበ እስራኤል እንዲህ ብሏል፡

> **አምላክህ እግዚአብሔር ይፈትንህ ዘንድ፥ በልብህም ያለውን ትእዛዙን ትጠብቅ ወይም አትጠብቅ እንደሆነ ያውቅ ዘንድ፥ ሊያስጨንቅህ በእነዚህ በአርባ ዓመታት በምድረ በዳ የመራህን መንገድ ሁሉ አስብ (ዘዳግም 8፡2)።**

ከቅዱሳት መጻሕፍት በግልጽ እንደምንረዳው እግዚአብሔር የሰዎችን ሁሉ ልብ ጨምሮ ሁሉን ነገር በትክክል ያውቃል፡፡ ሆኖም ይህና ሌሎችም ተመሳሳይ ምንባቦች እንደሚነግሩን፣ በታሪክ ዘመናት ውስጥ እግዚአብሔር ከህዝቦቹ ጋር በሚኖረው መስተጋብር፣ በልባችን ውስጥ ያለውን ነገር ገልጦ ለማሳየት ወይም ለማስረገጥ፣ ደግሞ ደጋግሞ ፈታኝ ሁኔታዎችን ይጠቀማል የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ያረጋግጡልናል፡፡

ያዕቆብ መመሪያ ሲሰጥ፣ ተደራሲያኑ የሚያልፉባቸው ፈተናዎች እምነታቸውን የሚፈትኑ ስለመሆናቸው ብቻ አውስቶ አያበቃም፡፡ በተጨማሪም ፈተናዎቻቸው ጽናትን እንዲያስገኙላቸው ታስበው እንደሚቀረፁም ያመለክታል፡፡

ጽናት

ያዕቆብ መፈተን ጽናትን እንደሚያስገኝ በሚጽፍበት ወቅት የተጠቀመው የግሪክ ቃል *hupomoné* (ὑπομονή) የተሰኘው ነው፡፡ ልክ "perseverance" እንደተሰኘው የእንግሊዝኛ ቃል፣ *hupomoné* የተሰኘውም ቃል ፈታኝ ሁኔታን መቋቋም የሚል ፍቺ አለው፡፡ ስለዚህ፣ ፈተና ከልብ የሆነ እምነትን የሚያረጋግጥ ሲሆን ይህም የሚሆነው የእግዚአብሔርን ህዝብ እንዲጸናና ለክርስቶስ በተሰጠ እምነት እንዲቀጥል በማስቻል መሆኑን ያዕቆብ አብራርቷል፡፡

በጥቅል አነጋገር፣ አዲስ ኪዳን ስለ ክርስቲያናዊ ጽናት የሚያስተምረው ትምህርት ባለ ሁለት ፈርጅ ነው፡፡ በአንድ ጎኑ፣ ጽናት የእግዚአብሔር ጸጋ ስጦታ ነው፡፡ ሮሜ 6፡1-14 የመሳሰሉት ምንባቦች እንደሚያስተምሩን የክርስቶስ ተከታዮች በመከራ ውስጥ የሚጸኑበትን አቅም ያገኛሉ ምክንያቱም ክርስቶስን ከሙታን ያስነሳው፣ መንፈስ ቅዱስ፣ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስና በታማኝነትና በመታዘዝ እንድንጸና ስለሚያስችለን ነው፡፡ ስለዚህ፣ ጽናት የሰውን ጥረት ቢጠይቅም እንኳን፣ እኛ ግን መጽናት የምንችለው በውስጣችን በሚሠራው በእግዚአብሔር የማይቋረጥ ጸጋ አማካይነት መሆኑን ልናስታውስ ይገባናል፡፡

በሌላ በኩል ግን፣ አዲስ ኪዳን በተጨማሪም ለዘላለማዊ ድነት ጽናት እጅግ ወሳኝ መመዘኛ እንደሆነ በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ በሌላ አገላለጽ፣ ለድነት የሚያበቃ እምነት አምኛለሁ የሚሉ ሰዎች፣ በእምነታቸው የመጽናታቸው ነገር ለድርድር የሚቀርብ አይደለም ማለት ነው፡፡ ጳውሎስ በቆላስይስ 1፡22-23 የተናገረውን አድምጡ፡

> **ዒሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ። ይህም፥ ተመሥርታችሁና ተደላድላችሁ ከሰማችሁትም ከወንጌል ተስፋ ሳትናወጡ፥ በሃይማኖት ጸንታችሁ ብትኖሩ ይሆናል፤ ያም ወንጌል ከሰማይ በታች ባለው ፍጥረት ሁሉ ዘንድ የተሰበከ ነው፥ (ቆላስይስ 1፡22-23)**

በዚህ ስፍራ ጳውሎስ አስረግጦ የሚናገረው የቆላስይስ ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር እንደታረቁ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ እውነተኛ ሊሆን የሚችለው በእምነታቸው ጸንተው ከገፉበት ብቻ እንደሆነ በእርግጠኝነት ሊያውቁ ይገባል፡፡ ይህ ጽናትን መመዘኛ አድርጎ የማስቀመጥ ጉዳይ በእግዚአብሔር ጸጋ ከሚገኘው የድነት መልእክት ጋር የሚጻረር አይደለም፡፡ ይልቁኑ፣ ከወንጌል የሚመነጭ ተስፋ ነው፡፡

ያዕቆብ በመመሪያው ውስጥ የሚያወሳው የእምነት መፈተን መጽናትን እንደሚያስገኝ ብቻ አለመሆኑን ነው፡፡ በተጨማሪም የሚያወሳው ከጽናት ስለሚመነጨውም ብስለት ነው፡፡

ብስለት

> **የያዕቆብ መጽሐፍ በጥቅሉ የሚያወሳው ስለ ክርስቲያናዊ ብስለት ነው፡፡ አንዳንዶች መጽሐፉን የሚቀርቡት ስለ ህገኝነት የሚያወሳ መጽሐፍ እንደሆነ በማሰብ ነው፤ ማለትም ስለ ህግጋት፣ እኔ ላደርግ የሚገባኝን ምንም ሳላዘባ ስለ ማድረግ የሚያወሳ እንደሆነ አድርገው ያስቡታል፡፡ መጽሐፉ ግን በእውነት ዒላማ ያደረገው እናንተ እንደ ክርስቲያን፣ በተለይም ደግሞ አሁን በምንኖርበት ዓለም በሚያጋጥሙን ፈርጀ ብዙ ፈተናዎች ውስጥ እንደ ክርስቲያን ለመኖር በሚስችል መልክ እንድታድጉ ማገዝን ነው፡፡ በዘመኑ በቤተክርስቲያን ውስጥ መገኘት ፈተና ነበር፤ ያዕቆብ ያንን ያውቃል፡፡ ይህን በመሰለው ዓለም ውስጥ፣ በቤተክርስቲያን በጽናት ለመኖር፣ በዚህች ቤተክርስቲያን ውስጥ አብቦ ለመኖር ብስለት ማለትም ሙሉና ፍጹም መሆን እጅግ ያስፈልጋል፡፡ ይህንን መሳዩን ሕይወት እንዴት በበሳልነት መምራት እንደምትችሉ፣ ዓለም ምንም ትምሰል ምንም፣ ዲያቢሎስም ምንማ ያምጣ ምንም፣ ሥጋም መንገዳችሁን ለማደናቀፍ ምንም ያስቀምጥ ምን፤ ያንን እንዴት ማለፍ እንደምትችሉ ያዕቆብ አስረግጦ ይናገራል፡፡ ከያዕቆብ አጻጻፍ በጣም የምትገረሙበት ነገር ቢኖር፣ የሚጀምረው በመከራ መሆኑ ነው፡፡ መከራ ማለት የማንጠሪያ ሳህን ዓይነት ነው፣ አውዱ ያንን ይመስላል፤ በሌላ ቋንቋ ክርስቲያናዊ ብስለት የሚዳብርበት ጅምናዚየም ነው ማለት ይቻላል፡፡ እምነታችሁ ተኮትኩቶ የሚያድግበት እና ለመጪው ሕይወት ዝግጁ የሚሆንበት ነው፡፡ በመከራ ስትጸኑ፣ በፈተና ውስጥ ስታልፉ እና ጸንታችሁ ስትቆሙ፣ እምነታችሁም በመንፈሱ አማካይት በዓለም ውስጥ ተገልጦ ሲታይ፣ እምነታችሁ በክርስቶስ፣ በህግጋቱና በጥበቡ አማካይነት እየጨመረ በመሄድ ወደፊት ሊመጣ ላለው ፈተና ዝግጁና ብቁ እየሆነ ይመጣል፡፡**
>
> **- ዶ/ር ቶማስ ኤል. ኬን**

ያዕቆብ 1፡4 የሚናገረውን በድጋሚ እንመልከት፡

> **ትዕግሥትም ምንም የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም (ያዕቆብ 1፡4)።**

መከራና ጽናት ብስለትን የሚያስገኙ እስከሆኑ ድረስ፣ ጽናት ሥራውን እንዲፈጽም ያዕቆብ ለተደራሲያኑ ይነግራቸዋል፡፡ ጽናት በሳል፣ ፍጹማንና ምሉዓን፣ አንዳችም የማይጎድላቸው ያደርጋቸዋል፡፡

እንግዲህ አሁን፣ በጣም ጥንቃቄ ማድረግ ያሻናል፡፡ በዚህ ዓለም ሕይወታችን ወደ ግብረገባዊ የንፅህና ሙላት፣ አንዳችም ወደማይጎድለው ፍፅምና እንደርሳለን የሚል ሃሳብ ያዕቆብ እንደሌለው ልናውቅ ይገባናል፡፡ 1ኛ ዮሐንስ 1፡8 ከመሳሰሉ ምንባቦች እንደምንረዳው፣ "ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም፡፡" ያዕቆብ በልቡናው የያዘው ሃሳብ፣ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ስንጸና፣ ክርስቶስ ዳግመኛ ሲመለስ በፍርድ ወንበር ፊት ስንቀርብ፣ ብቁ የማያደርገን ምንም ነገር አይኖርም፣ አንዳች የሚጎድለን ነገር አይኖርም የሚለውን ነው፡፡

ስለ መፈተን፣ ስለ ጽናትና ስለ ብስለት መመሪያ ከሰጠ በኋላ፣ ይህ ሂደት ሲጠናቀቅ ታላቅ ብድራት እንደሚጠብቃቸው ያዕቆብ ያመለክታል፡፡

ብድራት

ያዕቆብ በ1፡12 ውስጥ ይህንን ብድራት እንዲህ አስቀምጦታል፡

> **በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ከተፈተነ በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወትን አክሊል ይቀበላልና (ያዕቆብ 1፡12)።**

ያዕቆብ በዚህ ስፍራ እንዳብራራው፣ በፈተና የሚጸና ሰው፣ እምነቱ ይበልጥ ወደሚፈተንበት እርከን ውስጥ ይገባል፡፡ እነርሱም የሕይወትን አክሊል ይቀበላሉ፣ ይህም የሕይወት አክሊል፣ በእግዚአብሔር (በጌታ) የከበረ መንግሥት ውስጥ ለሚወድዱት ተስፋ የሰጠው ነው፡፡ እነዚህን አመለካከቶች አንድ ላይ ስናመጣቸው፣ ልብን ሰርስሮ የሚገባ ማሳሰቢያ ሰጪ ጥበብን ያዕቆብ ለተደራሲያኑ የሚያጋራ መሆኑን ያሳዩናል፡፡ የሚያጋጥሟቸውን ፈተናዎች የሚረዱበትን መመሪያም ያቀርብላቸዋል፡፡ እንደ እውነቱ፣ እያንዳንዱ ፈተና የእግዚአብሔር ስጦታ ሲሆን፣ ዓላማውም ፍጻሜአቸውን መልካም ማድረግ ነው፡፡

> **ያዕቆብ ገና ከደብዳቤው ጅማሬ አንስቶ ከተናገረባቸው ነገሮች አንዱ ደግሞም ከዳር እስከዳር ሲዘልቅ የምናገኘው ሃሳብ በመከራ ውስጥ የመጽናት ሃሳብ ነው፡፡ ያም ጉዳይ በእውነት ወደ ክርስቲያናዊ ብስለት የሚደርስ ነው ብሎ የተናገረበት ጉዳይ ነው፡፡ በምዕራፍ 1 ጅማሬ ላይ፣ "ወንድሞቼ ሆይ፥ ... ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት" ብሏቸዋል፡፡ ከዚያም ምክንያቱን ሲስረዳቸው፣ "የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ" ይላቸዋል፡፡ ከዚያም በመቀጠል፣ "ትዕግሥትም ምንም የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም።" ይላቸዋል፡፡ ስለዚህም፣ ምናልባት እኛ መከራ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ያለመሆኑ ምልክት እንደሆነ እንቆጥር ይሆናል፣ ያዕቆብ ግን መከራን የሚመለከተው፣ እግዚአብሔር ከመከራ ሲታደገን ብቻ ሳይሆን በመከራም ውስጥ እያሳለፈን እርሱ የሚፈልጋቸው ዓይነት ሰዎች አድርጎ እንደሚሠራበት ነው፡፡ በብስለት የምናድግበት ስፍራም በእርግጥ እርሱ ነው፡፡ በነገሩ በመግፋትም በቁጥር 12 ላይ፣ በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ከተፈተነ በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወትን አክሊል ይቀበላልና። ይላል፡፡ እናም ስለ መከራ ያለንን አስተሳሰብ የሚስለውጥ የተለየ አመለካከት ያቀርብልናል፡፡ ይህ ነገር አይድረስብን የምንለው ወይም ገሸሽ የምናደርገው ነገር ሊሆን አይገባም፡፡ በእኛ ባህል ስኬት ማለት መከራን ገሸሽ ማድረግ ነው፣ በዚህ ስፍራ የተገለጠው ግን የማደግን እድል የምናገኝበት ሕይወት እንደሆነ ነው፡፡ ስንጠቀልለውም ክርስቲያናዊ ብስለት የሚነጠርበት ማቅለጫ ነው፡፡**
>
> - **ሬቨረንድ ዶ/ር ቱርማን ዊሊያምስ**

ያዕቆብ ተደራሲኑ በሚያልፉበት ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ይጠቅማቸው ዘንድ ማሳሰቢያ ሰጪ በሆነው ጥበብ ላይ በማትኮር ይጽፍላቸዋል፡፡ በተጨማሪም መመሪያም ይሰጣቸዋል፡፡ አሁን ግን፣ ማሳሰቢያዊ የጥበብ ጎዳና እምነትን እንዴት እንደሚጠይቅ ወደመመልከቱ እንሸጋገር፡፡

እምነት

ተደራሲያኑ በፈተናዎቻቸው ዘንድ ሊያደርጉ ስለሚገባቸው ነገር ያዕቆብ ስላስጨበጣቸው ግንዛቤ ስናስብ፣ ከተለመዱ ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ጋር ይመሳሰላል፡፡ ነገር ግን በሕይወታችን ችግሮች በሚገጥሙን ወቅት፣ በቶሎ አቅማችን ድክም ይላል ከዚያም መሠረታዊ የሆኑትን ክርስቲያናዊ እምነቶችን እንኳን ጠብቆ መቆየት እጅግ ፈታኝ ሲሆንብን ራሳችንን እናገኘዋለን፡፡ ያዕቆብም እንዲሁ ተደራሲያኑ በተመሳሳይ ችግር ውስጥ ሳይገቡ እንደማይቀሩ ያስባል፡፡ ስለዚህም፣ ያዕቆብ ፈጠን ብለው ያስተላለፈላቸውን መረዳቶች የራሳቸው እንዲያደርጉ ያመለክታቸዋል ያንንም የሚያደርጉት ፈጥነው በእግዚአብሔር ላይ ወደነበራቸው እምነት በመመለስ ነው፡፡ በያዕቆብ 1፡5 ውስጥ እንዲህ ተጽፏል፡

ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል (ያዕቆብ 1፡5)።

በመከራዎቻችን ወቅት እግዚአብሔር ያለውን ስውር ዓላማ ለመረዳት የሚያስችለንን ጥበብ መቀበል የምንፈልግ ከሆነ፣ "እግዚአብሔርን ስለዚያ ልንጠይቅ" እንደሚገባ ያዕቆብ ያውቃል፡፡ ይህንን ተከትሎ ግን፣ በ1፡6-8 ውስጥ፣ ጥበብን ለማግኘት በእምነት የሆነ ጸሎት አስፈላጊ መሆኑን ያዕቆብ እንዲህ ያያይዘዋል፡፡

ነገር ግን በምንም ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን፤ የሚጠራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባሕርን ማዕበል ይመስላልና።
ሁለት አሳብ ላለው በመንገዱም ሁሉ ለሚወላውል ለዚያ ሰው ከጌታ ዘንድ አንዳች እንዲያገኝ አይምሰለው (ያዕቆብ 1፡6-8)።

በዚህ ስፍራ እንደምናየው፣ ጥበብን ለማግኘት የምናቀርበው ጸሎት በእምነት ሊቀርብ እንደሚገባ ያዕቆብ ያሳስባል፡፡ ያ ካልሆነ ግን በመንታ ልብ የምንዋልል ሰዎች እንሆናለን፡፡

እንደ አለመታደል ሆኖ ግን፣ በርካታ እውነተኛ የተባሉ ክርስቲያኖች እንኳን ያዕቆብ ባልተከፋፈለ ልብ በእምነት ስለመጠየቅ ያስተላለፈውን መልእክት በተሳሳተ መንገድ ይረዱታል፡፡ ነገሩም እንዲህ ነው፡፡ በእምነት በምናቀርበው ጸሎት መመካት እንደምንችል ያዕቆብ ተናግሯል ብለው ያስባሉ፡፡ እኛ የክርስቶስ ተከታዮች፣ በቂ እምነት ካለን፣ እግዚአብሔር ጸሎታችንን እኛ በምንፈልገው መንገድ ይመልስልናል ብለን ደግመን ደጋግመን እናስባለን፡፡ ያዕቆብ በልቡናው የያዘው እውነት ግን ከዚህ የራቀ ነው፡፡ ለያዕቆብ፣ "በእምነት መጠየቅ" ማለት "ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን" ማለት ነው፡፡ ይህንንም የምናውቀው ያዕቆብ "በእምነት መጠየቅን" "የወላዋይነት" ተቃራኒ አድርጎ ስለገለጸው ነው፡፡ ለያዕቆብ ወላዋይነት ማለት በእግዚአብሔር ላይ እጅግ በብርቱ ማመፅ ነው፡፡ በ1፡13-14 ውስጥ ይህንን የተሳሳተ ግንዛቤ ያዕቆብ እንዴት እንደገለጸው እናድምጥ፡

ማንም ሲፈተን፦ በእግዚአብሔር እፈተናለሁ አይበል፤ እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንምና፤ እርሱ ራሱስ ማንንም አይፈትንም።
ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል (ያዕቆብ 1፡13-14)።

በዚህ ስፍራ "ሲፈተን" ተብሎ የተተረጎመው ቃል የግሪኩ አገባብ *peirazō* (πειράζω) የሚል ግስ ሲሆን፣ ይኸው ቃል በ1፡2 ውስጥ "መፈተን" ተብሎ ተተርጉሟል፡፡ ያዕቆብ እያለ ያለው ግን እግዚአብሔር ራሱ ማንንም አይፈትንም ነው፡፡ ይህ ትርጓሜ በትክክል የሚያመለክተው በዘመኑ በስፋት አገልግሎት ላይ ይውል የነበረውን *autós* (αὐτός) የተሰኘውን የግሪክኛ ተውላጠ ስም ወይም "ራሱ" የሚለውን ቃል ነው፡ አግዚአብሔር "አይፈትንም" ወይም "ማንንም" አይፈትንም ብቻ አይደለም የሚለው፡፡ በቀጥታ እያለ ያለው "እግዚአብሔር ራሱ ማንንም አይፈትንም" ነው፡፡

ከኢዮብ መጽሐፍ የመጀመሪያ ምዕራፍ እንደምንማረው፣ እግዚአብሔር ሁሉንም ፈተናዎች፣ መከራዎችና ተግዳሮቶች ይቆጣጠራል፡፡ ሆኖም፣ በሰማያዊ የፍርድ ወንበር ፊት ግን፣ በኢዮብ መከራዎች ውስጥ እግዚአብሔር ያለው ዓላማ ለኢዮብ መልካም እንጂ ለጉዳት እንዳልሆነ ግልፅ ብሎ ታይቷል፡፡ ፈተናውን ወደ ፈተና ለመክተት ሊጠቀምበት የፈለገው እግዚአብሔር ሳይሆን ሰይጣን ነበር፡፡

ስለዚህ፣ ጥበብን እንዲሰጠን በእምነት የመለመኑና ያለማወላወሉ ጉዳይ እጅግ መሠረታዊ ከሆኑት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶች መካከል ቀዳሚ የሆነውን የእግዚአብሔርን መልካምነት የሚያጸና ሃሳብ ነው፡፡ ፈታኝ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ከእርሱ ጥበብን ለመቀበል ስንናፍቅ የእግዚአብሔርን መልካምነት በፍጹም መጠራጠር አይገባንም፡፡ ይህ ካልሆነ ግን፣ እግዚአብሔር ጥበብን እንደሚሰጠን የምናምንበት ምንም ምክንያት አይኖርም፡፡ ያዕቆብ በ1፡17 እንደገለጸው፡

በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፥ መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ (ያዕቆብ 1፡17)።

እግዚአብሔር "የብርሃናት አባት" ነው፡፡ እርሱ የሚሰጠንም ስጦታ "በጎ" እና "ፍጹም" ነው፡፡ ስለዚህ፣ መከራችንን አስመልክቶ ያለው ዓላማ ሁልጊዜም ቢሆን "በጎ" እና "ፍጹም" ነው፡፡ ማሳሰቢያ ሰጪ የሆነውን የጥበብን ጎዳና በምንከተልበት ወቅት ስለ እምነታችን ሊኖረን የሚገባው ቁርጠኛ አቋም ይህ ነው፡፡

በያዕቆብ መጽሐፍ ውስጥ ስለሚገኙት ስለ ሁለቱ የጥበብ መንገዶች ስናጠና፣ ያዕቆብ በማሳሰቢያ ሰጪ ጥበብ ላይ ያደረገውን ትኩረት ተመልክተናል፡፡ አሁን ደግሞ ወደ ሁለተኛው ርዕሳችን የምንሸጋገርበት ወቅት ላይ ደርሰናል፡፡ ያም ርዕስ፤ ተግባራዊ ጥበብ ነው፡፡ ይህ የአዲሰ ኪዳን መጽሐፍ ጥበብን በተግባር ስለመግለጥ ምን የሚናገረው ነገር አለ?

ተግባራዊ ጥበብ

በአንድም ሆነ በሌላ ወቅት እጅግ ታዋቂ የሆኑ ሰዎችን የማግኘት ዕድል ሁላችንም ይገጥመናል፡፡ ከሌሎች ሰዎች የተሰወሩ ለእነርሱ ግን ግልጥ የሆኑ በርካታ ነገሮችን በማንሳት ሰዎችን ሁሉ ያስደምማሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ግን፣ እነዚያው ሰዎች ስለ ተግባራዊ ሕይወት ምንም እውቀት የሌላቸው ሆነው ይገኛሉ፡፡ የሚያውቁትን እውቀት ወደ ትክክለኛ ተግባርና ዝንባሌ መለወጥ ያዳግታቸዋል፡፡ ያዕቆብ በመጽሐፉ ውስጥ የዳሰሰው ይህንን መሳዩን ጉዳይ እነደሆነ በብዙ መንገዶች እናስተውላለን፡፡ ቀደም ብለን እንዳየነው፣ መልእክቱን የሚከፍተው ማሳሰቢያ ሰጪ ስለሆነው ጥበብ አፅንዖት በመስጠት ነው፡፡ በሚያጋጥሙን ፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ እግዚአብሔር ያለውን የተሰወረ ዓላማ መገንዘብ ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ያውቃል፡፡ በተጨማሪም ደግሞ እነዚያን ያወቅናቸውን እውቀቶች በተግባርና በትክክለኛ ዝንባሌ መግለጥ እንደሚያስፈልግ ያመለከተበትን ተግባራዊ ጥበብም ዳስሷል፡፡

ነገሩን ላለማወሳሰብና ቀለል ለማድረግ፣ ይህንን የተግባራዊ ጥበብ ሃሳብ ቀደም ብለን ከዳሰስናቸው ሃሳቦች ጋር ተዛማጅ በሆነ መንገድ እንመለከተዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ በተግባር ስለሚገለጥ ጥበብ አስፈላጊነት እንዳስሳለን፡፡ ሁለተኛ፣ ያዕቆብ ለተደራሲያኑ እንዴት መመሪያ እንደሰጠ እናያለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ በእምነትና በተግባር መካከል ስላለው ግንኙነት እንመለከታለን፡፡ አስቀድመን ያዕቆብ ለተደራሲያኑ ስለሚያስፈልጋቸው የተግባራዊ ጥበብ ፍላጎት በመመልከት እንጀምር፡፡

ፍላጎት

ቀደም ብለን እንዳየነው፣ ያዕቆብ "ጥበብ" እና "ጠቢብ" የተሰኙትን ቃሎች የተጠቀመባቸው በሁለት አውዶች ውስጥ ብቻ ነው፡፡ ከእነዚህ የመጀመሪያው የሚገኘው በ1፡2-18 ውስጥ ሲሆን ያዕቆብ አፅንዖት ያደረገውም በማሳሰቢያ ሰጪ ጥበብ ላይ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በ3፡13-18 የሚገኝ ሲሆን ያዕቆብ አፅንዖት ያደረገበትም ጥበብን በተግባር ላይ ስለማዋል ነው፡፡

> **የያዕቆብ መልእክት በጣም ተግባራዊ መልእክት ነው፡፡ ሰዎች እናምናለን ብለው የሚናገሩለትን ነገር በግባር እንዲገልጡት በእርግጥ ይፈልጋል፡፡ ታዲያ ይህንን ከወዴት አመጣው? እንግዲህ ምላሹ የሚሆነው፣ ኢየሱስ ራሱ ነው፡፡ ማለቴ፣ ቤትን በዐለት ወይም በአሸዋ ላይ ስለ መገንባት የሚያወሱ ምሳሌዎችን ኢየሱስ ተናግሯል፡፡ ልዩነት የሚፈጥረው ጉዳይ ደግሞ፣ "እኔ ያዘዝኳችሁን ታደርጋላችሁን? ያስተማርኳችሁን ተግባራዊ ታደርጋላችሁን?" የሚለው ነው፡፡ ኢየሱስ ማየት የሚፈልገው ደግሞ ይህንን ነው፡፡ ሰዎች የሚያምኑበትን ነገር ተግባራዊ ሲደርጉት ማየት ናፍቆቱ ነበር፡፡ እንደምታውቁትም፣ ፈሪሳውያንንም አስመልክቶ፣ "የሚናገሩትን በጥንቃቄ ጠብቁት ነገር ግን የሚያደርጉትን በተግባር ላይ ስለማያውሉት ተግባራቸውን ግን አትመልከቱ" በማለት ማስጠንቀቂያ ሰጥቷቸዋል፡፡ ስለዚህ፣ ኢየሱስ ነገሮችን በተግባር መግለጥን አስመልክቶ አቋሙ እጅግ ጥብቅ ነው፣ እንግዲያው፣ እኔ እንደማስበው፣ ያዕቆብም በአንድ ወገን ወንድሙን፣ ኢየሱስን በደንብ መስሎታል ስለዚህም ጉዳዩ እጅግ ብርቱ እንደሆነ የተናገረው ለዚህ ነው፡፡ እርግጥ ነው፣ ሌላ ሁለተኛ ምክንያትም ይኖራል፣ ምናልባትም ጉዳዩ እኛን ከመጀመሪዬቱ ቤ/ክ ጋር ሳንመሳሰል አንቀርም፡፡ በያዕቆብ ዘመን የነበሩ አይሁድ ክርስቲያኖች የኢየሱስን ሕይወት በመኖር ማሳየት ተስኖአቸው ነበር፣ ምናልባትም ያዕቆብ የጉዳዩን አደገኝነት ማስተዋል የጀመረ ይመስላል ምክንያቱም ይህ ዓይነቱ ሕይወት የክርስቲያን ምስክርነትን እጅግ የሚያጠፋ ነው፡፡ ታውቃላችሁ፣ ስለ**

ኢየሱስ እነዚህን የመሳሰሉ ትልልቅ አስተምህሮዎች ያውቃሉ፣ ነገር ግን በእውነት ተግባራዊ ሊያደርጓቸው አይፈልጉም፣ "የምትሰብኩትን በተግባር ላይ አታውሉትም" የሚለው ወቀሳ የሚመጣው እዚህ ላይ ነው፣ ያም ደግሞ ለክርስቲያናዊ መልእክት ክፉ ስም ያሰጣል ... ኢየሱም "ፍጹማን ሁኑ" ያለው ለዚህ ነበር፣ ያዕቆብም ያንኑ አስተምህሮ ይደግመዋል፡፡ ሰዎች ነገሮችን በተግባር እንዲገልጡ ይፈልጋል፣ እኛም የምናስተውለው አጽንዖት ይኸው ነው፡፡

- **ዶ/ር ፒተር ዎከር**

ያዕቆብ ስለ ተግባራዊ ጥበብ መሠረታዊ መርህ በ3፡13 ውስጥ የተናገረውን እስኪ እናድምጥ፡

> **ከእናንተ ጥበበኛና አስተዋይ ማን ነው? በመልካም አንዋዋሩ ስራውን በጥበብ የዋህነት ያሳይ (ያዕቆብ 3፡13)።**

ከያዕቆብ ተደራሲያን መካከል አብዛኞቹ ከብሉይ ኪዳን ጋር ቀረቤታ ያላቸው አይሁድ ክርስቲያኖች እንደሆኑ ካስታወስን፣ ቢያንስ ጥቂቶቹ "ጥበበኛና አስተዋይ" ነን ብለው ሊናገሩ እንደሚችሉ መገንዘብ አዳጋች አይሆንብንም፡፡ ያዕቆብ እያሳሰበ ያለው ግን ይህ አዋጅ እውነተኛ ከሆነ "በመልካም አኗኗራቸው ሊገልጡት ይገባል" የሚለውን ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ፣ ተግባራዊ ጥበብ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በብሉይ ኪዳን አስተምህሮዎች፣ በተለይም በመጽሐፈ ምሳሌ በጉልህ እንደተቀመጠው፣ የጥበብ ጉዳይ ልብን ሰርስሮ ከሚገባ ነገረ-መለኮታዊ መረዳቶች እጅግ የዘለለ ፋይዳ እንዳለው ያዕቆብ ጠንቅቆ ያውቃል፡፡

ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚገኘውን መረዳት በሙሉ ልባቸው የሚቀበሉ ሰዎች "ከጥበብ የሚመነጨውን" "መልካም አኗኗር" ያሳያሉ፡፡ ያዕቆብ በተጨማሪም ያ መልካም ሕይወት ትርጓሜው እንደሚያሳየን፣"ተግባር" እና "ሥራን" የሚያካትት እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ይህም አንዳንድ የባህርይ መገለጫዎችን ለምሳሌ እንደ "ትኅትና" የመሳሰሉትንም ያስከትላል፡፡ እንደምንመለከተው፣ ትክክለኛ ተግባሮችና አስተሳሰቦች ሁለቱም ለተግባራዊ ጥበብ ወሳኝነት አላቸው፡፡

የተግባራዊ ጥበብን አስፈላጊነት በበለጠ ሁኔታ ለማብራራት ሲል፣ በዚህ ትምህርታችን መጀመሪያ ላይ ያነሳናቸውን ሁለት ዓይነት ጥበቦች ያዕቆብ በማነጻጸር ያቀርባል፡፡ አስቀድሞ ያመለከተው ምድራዊ ጥበብን ነው፡፡ በማስከተል ደግሞ፣ ስለ ሰማያዊ ጥበብ ተናግሯል፡፡ አስቀድመንም ስለ ምድራዊ ጥበብ እንመልከት፡፡

ምድራዊ ጥበብ

በ3፡14-16 ውስጥ፣ ስለ ምድራዊ ጥበብ ይህንን መግለጫ እናገኛለን፡

> **ነገር ግን መራራ ቅንዓትና አድመኛነት በልባችሁ ቢኖርባችሁ፥ አትመኩ በእውነትም ላይ አትዋሹ። ይህ ጥበብ ከላይ የሚወርድ አይደለም፤ ነገር ግን የምድር ነው፥ የሥጋም ነው፥ የአጋንንትም ነው፤ ቅንዓትና አድመኛነት ባሉበት ስፍራ በዚያ ሁከትና ክፉ ስራ ሁሉ አሉና (ያዕቆብ 3፡14-16)።**

በዚህ ትምህርት የመጀመሪያ አጋማሽ ውስጥ እንደተመለከትነው፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ በባለጠጎችና በድሆች መካከል ተፈጥሮ ስለነበረው ብጥብጥ ያዕቆብ እጅግ ግድ ብሎት እንደነበር አይተናል፡፡ እናም በ3፡14 ውስጥ፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙዎቹ "መራራ ቅንዓትና በራስ መመካት በልባቸው ውስጥ የመሙላቱን" እውነታ ይፋ ያደርገዋል፡፡ እንደ ቁር 15 አገላለጽ ደግሞ፣ ቢያንስ ጥቂቶቹ ይህንን ተግባራቸውን "ጥበብ" በማለት ሊያጸድቁት ይሞክሩ ነበር፡፡ ያዕቆብ ግን በሚያደርጉት ነገር ወይም ሊያብራራላቸው የሚፈልገውን እውነት በመካዳቸው ሊመኩ እንደማይገባ ያስጠነቅቃቸዋል፡፡

በመጀመሪያዩቱ ቤተክርስቲያን ውስጥ በድሆችና በባለጠጎች መካከል ስለ ነበረው ግጭት ያዕቆብ ያንን ያህል ግድ የመሰኘቱ ጉዳይ ለምን እንደሆነ በዘመናችን የሚገኙ በርካታ ክርስቲያኖች በትክክል ለመገንዘብ ይቸገራሉ፡፡ በዘመናችን ያለችውም ቤተክርስቲያኝ በውስጧ ድሆችንና ባለጠጎችን የማካተቷ ነገር እንደቀጠለ ነው፡፡ ይህም በአንዳንድ አገሮች ያሉትን ክርስቲያኖች ስናስተያይ የምናስተውለው ነው፡፡ በዘመነኛዋ ቤተክርስቲያን ግን፣ ከመጀመሪያዋ ቤተክርስቲን ተቃራኒ በሆነ መንገድ፣ የአጥቢያ ጉባዔዎች በአብዛኛው ወደ አምሳያዎቻቸው የማድላት አዝማሚያ ይታይባቸዋል፡፡ ባለጠጋ ክርስቲኖች እነርሱን መሳይ ባለጠጎች ወደሚገኙባቸው ቤተክርስቲያናት፣ ድሆችም ድሆች ወዳሉባቸው ቤተክርስቲያናት ወደመሄዱ ያዘነብላሉ፡፡ ግን በእናንተ አጥቢያ ውስጥ በጣም ድሆች ደግሞም በጣም ባለጠጎች ቢኖሩ ብላችሁ ለማሰብ ሞክሩ፡፡ ምን

ዓይነት ብርቱ ግጭት ይፈጠር ይሆን? አንዳንዶች ወደ ቤተክርስቲያን የሚመጡት ያረጁ ልብሶችን ለብሰው፣ የሚቀጥለውን ምግባቸውን ከየት ሊያገኙ እንደሚችሉ ሳያውቁ ሲሆን፣ የተቀሩት ደግሞ በዚው ተመሳሳይ አዳራሽ ውስጥ ውድ ልብሶችን ለብሰው፣ ኪሶቻቸው በገንዘብ ታጭቀው ይቀመጣሉ፡፡ በእናንተ አጥቢያ ውስጥ ይህ ጉዳይ እውን ቢሆን፣ ቤተክርስቲያናችሁ ብጥብጥ ውስጥ ትወድቃለች፡፡

በድሆችና በባለጠጎች መካከል የነበሩ ግጭቶች በያዕቆብ ዘመን በነበሩ ቤተክርስቲያናት ውስጥ ትልልቅ ውድመቶችን አስከትለው ነበር፡፡ በግልጽ ይታይ አንደነበረው፣ በባለጠጎቹ እየቀኑም እንኳን፣ ድሆቹ ራሳቸውን እንደ ጻድቅና ጠቢብ ይቆጥሩ ነበር፡፡ ምክንያቱም በብሉይ ኪዳን በመጽሐፈ ምሳሌ ውስጥ ባለጠጎች ለድሆች ቸር እንዲሆኑ እንደታዘዙ ያውቃሉና ነው፡፡ ስለዚህ፣ ክርስቲያን ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ያላቸውን ሊያካፍሉ ይገባል ብለው ያስባሉ፡፡ ባለጠጎቹም ደግሞ ራስ ወዳድ እየሆኑ እንኳን፣ ራሳቸውን ጻድቅና ጠቢብ አድርገው ይቆጥራሉ፡፡ ምናልባትም በብሉይ ኪዳን በምሳሌ ውስጥ ድህነት ከስንፍና የሚመነጭ ነው ብልጥግና ደግሞ የብርቱ ጥረት ሽልማት ነው የሚለውን ሊጠቅሱ ይችላሉ፡፡

ይህን መሳዩ ጥበብ ተብዬ ጉዳይ በሳሳተ መንገድ ከመመራትና ከመሳሳት እጅግ የከፋ እንደሆነ ያዕቆብ ያመለክታል፡፡ ምድራዊ፣ ከመንፈሳዊነት የጎደለ፣ ወይም ተፈጥሮአዊ እና አጋንንታዊ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ አጋንንታዊ መሠረት እንዳለው መገንዘብ ስህተት የሌለበት ነው፡፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ የስርዓት የለሽነትንና የተለያዩ ክፉ ልምምዶች ምንጭ እርሱ ነው፡፡

> **ራሳቸውን በራሳቸው ዓይን ጠቢብ አድርገው የሚቆጥሩ ሰዎችን ሁሉም ሰው ያውቃቸዋል ብዬ አስባለሁ፣ ያን መሳዩ ጥበብ አብዛኛውን ጊዜ መደምደሚያው ትዕቢት፣ ጠላትነት፣ እና ከሌሎች ጋር ተቃራኒ ሆኖ የመገኘትን ተፈጥሮ የሚያላብስ ይሆናል፡፡ ያ ዓይነቱ ጥበብ ከእግዚአብሔር እንዳልሆነ ያዕቆብ ይናገራል፡፡ እውነታው እንደሚያስረግጥልን፣ ያ ዓይነቱ ጥበብ፣ ምድራዊው ጥበብ፣ ያዕቆብ ከታች የሆነ ብሎ የጠራው፣ አደገኛና ጥቅም የሌለው ብቻ ሳይሆን፣ እርሱ እንደገለጠው "አጋንንታዊ" ነው፡፡ በተቃራኒው ግን፣ ከእግዚአብሔር የሆነው ጥበብ ጌታን ከመፍራት የሚመነጭ፣ በውጤቱም፣ መለያው ትኅትና ሲሆን፤ መታወቂያውም ርኅራኄ፤ ለጌታ ታማኝ በመሆን ተለይቶ የሚታወቅ ሲሆን፣ ያም በውስጣቸው እየተገለጠ እንደሆነ የሚገነዘቡ ሰዎችም ያ ነገር ከእነርሱ የመነጨ እንዳልሆነ፣ ይልቁኑ እግዚአብሔር በቸርነቱ የሚሰጣቸው እንደሆነ የሚረዱበት ጥበብ እንደሆነ ያዕቆብ ይናገራል፡፡ ይህ ዓይነቱ ጥበብ ክርስቲያኖች፣ ማለትም የኢየሱስ ክርስቶስ፣ እጅግ ታላቅ የሆነው ጠቢብ፣ ከሰሎሞን እጅግ የሚበልጠው ጠቢብ ተከታዮች የሆኑ ሁሉ ሊኖራቸው የሚገባ ጥበብ ሲሆን፤ ይህን ዓይነቱን ጥበብ የእርሱ ተከታዮች በሕይወታቸው በተግባር ሊገልጡት የሚገባ ጥበብ ነው፡፡**
>
> - **ዶ/ር ስኮት ሬድ**

በስተመጨረሻም፣ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን በመካከሏ ከተፈጠረው ጦርነት የተነሳ፣ የእግዚአብሔርን ሥራ ልታስፋፋ ሲገባት፣ ተከፋፈለች፡፡ ያዕቆብ መልእክቱን የጻፈላቸው ማኅበረ-ምዕመናንም ከየትኛውም ነገር እጅግ አስበልጠው የእግዚአብሔርን ሥራ ለማፍረስ ሌት ከቀን በሚፈልጉት አጋንንቶች ጥቃት ውስጥ ወደቁ፡፡ ተደራሲያኑ የተግባራዊ ጥበብ ምክር እንደሚስፈልጋቸው እንዲያስብ ያዕቆብን ያነሳሳው ይህ ትልቅ ጥፋት ነው፡፡ ያዕቆብ አፍራሽ ሆነውንና ከዓለም የሆነውን ጥበብ በእጅጉ ከተቃወመ በኋላ፣ የተግባራዊ ጥበብን አስፈላጊነት አንስቶ ወዲያው የተሸጋገረው ሰማያዊ ጥበብ ብሎ የሰየመውን አማራጭ ወደማቅረቡ ነው፡፡

ሰማያዊ ጥበብ

በ3፡17 ውስጥ፣ ይህንን አዎንታዊ ሰማያዊ ጥበብ እንዲህ ይገልጸዋል፡

> **ላይኛይቱ ጥበብ ግን በመጀመሪያ ንጽሕት ናት፥ በኋላም ታራቂ፥ ገር፥ እሺ ባይ ምሕረትና በጎ ፍሬ የሞላባት፥ ጥርጥርና ግብዝነት የሌለባት ናት (ያዕቆብ 3፡17)።**

ያዕቆብ በዚህ ስፍራ በልቡ አስቀምጦ የሚያሳየን ከሰማይ የሆነችውን ጥበብ ሲሆን፣ ያም ማለት ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነች ጥበብ ማለት ነው፡፡ ይህች ጥበብ ሰላም ወዳድ፣ ገር፣ እሺ ባይ፣ ምህረትና በጎ ፍሬ የሞላባት፣ ልዩነት የሌለባት እና እውነተኛ ናት፡፡ በሌላ አገላለጽ፣ ከሰማይ የሆነችው ጥበብ በድህነትም ቢሆን በብልጥግና ሰበብ የሚፈጠር ቅንዓትንና ራስ ወዳድነትን በተሳሳተ መንገድ አያጸድቅም፡፡ ከእግዚአብሔር የሆነው እውነተኛ ጥበብ ለሰላም ያለን ፍቅር የሚያበረታታ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ሰዎችም ይህንን ሰላም ወዳድነት ሌሎችን ያከብራሉ፣ ለሌሎች ራሳቸውን ይሰጣሉ ደግሞም ምህረት ወዳድ ናቸው፡፡ በጎ ፍሬ ሚያፈሩና በሰዎች ወይም በቡድኖች መካከል አድልዎ የማያሳዩ ናቸው፡፡ እነዚህ ተግባሮችና ዝንባሌዎች ሊመነጩ የሚችሉት ለክርስቶስ ካለ እውነተኛ መሰጠት ነው፡፡

> **ከእግዚአብሔር የምትገኘውና ከላይ የሆነችው ጥበብ፣ ከላይ በመሆኗ ምክንያት፣ የእግዚአብሔር የራሱ ባህርያት ነጸብራቅ ናት፡፡ ያዕቆብም፣ ንጽሕት፣ ሰላም ወዳድ፣ ገር፣ በጎ ፍሬ የሞላባት፣ ምሕረት ወዳድ እና የማትዋዥቅ፣ እና እውነተኛ ወይም ግብዝነት የሌለባት በሌላ አገላለጽ፣ በእርግጥም የኢየሱስን ባህርይ የምታንጸባርቅ ናት በማለት ሃሳቡን ያስቀምጣል፡፡ ኢየሱስ ማለት ከላይ የዘረዘርናቸውን ሁሉ ነው፡፡ እንደ ያዕቆብ አነጋገር እነዚህ ነገሮች ማለት ሕይወትን በአንድ ጊዜ ወደላይ የሚያስተኩሱ፣ ስኬታማነትን የሚያጎናጽፉ፣ የምትኖርበትን ቤት ለውጠው በትልቅ ቤት እንድትኖር የሚደርጉ ናቸው ማለት አይደለም፣ ይልቁኑ እነዚህ ባህርያት ይላል ያዕቆብ፣ ጽድቅና ሰላም ናቸው፡፡ በሌላ አነጋገር፣ እውነተኛ ሰላም፣ ሰው ሁሉ የሚየውን ሰላም የሚያስገኙ ናቸው፡፡ ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ ሁሉም ሰው ሰላምን፣ አንዳች ጉድለት የሌለበትን ሕይወት፣ ምሉዕነትን እና ሰላምን በእጅጉ የሚናፍቅ መሆኑ ነው፡፡ ሰዎች እነዚህን ነገሮች ይፈልጋሉ፣ እነዚህንም የሚያገኙ የሚመስላቸው ከምድራዊ ጥበብ ነው፡፡ እንደ እውነቱ ግን ያንን የመሰለው ሰላም ሊገኝ የሚችለው ከላይ ከሆነችው ጥበብ ብቻ ሲሆን ያም የአንድን ሰው የብቻ ምጥቀት የሚያስገኝ ሳይሆን፣ ያዕቆብ በምዕራፍ 3 ቁጥር 13 እንደተናገረው፣ ገር፣ ትኑትና የራሱን ብልጽግና ሳይሆን ስለሌሎች ጤናማነትና የተሳካ ሕይወት ግድ እንዲሰኝ የሚያስችሉ ናቸው፡፡**
>
> **- ዶ/ር ዳን ማካርተኒ**

ያዕቆብ በ3፡18 ውስጥ ለተደራሲኑ እጅግ ታዋቂ የሆነውን ምሳሌ ይጠቅስላቸዋል፡፡

> **የጽድቅም ፍሬ ሰላምን ለሚያደርጉት ሰዎች በሰላም ይዘራል (ያዕቆብ 3፡18)።**

ልክ ኢየሱስ በማቴዎስ 5፡9 ውስጥ የሚያስተራርቁ ሰዎችን እንደባረከ ሁሉ፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ድሆችም ሆኑ ባለጠጎች በቤተክርስቲያን ውስጥ እርቅንና ሰላምን የሚያመጡ እስከሆኑ ድረስ የጽድቃቸውን ብድራት እንደሚቀበሉ ያዕቆብ ግልጽ አድርጎ ያስቀምጣል፡፡

እስከአሁን በተጓዝነው ጉዞ፣ ስለ ተግባራዊ ጥበብ ደግሞም ያዕቆብ በመልእክቱ ውስጥ በዚህ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ ይህንን ያህል ትኩረት እንዲሰጥ ምን እንዳነሳሳው ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ የእግዚአብሔርን ጥበብ በተግባር ላይ እንዴት ሊያውሉት እንደሚገባ ወደሰጣቸው መመሪያ እንሸጋገራለን፡፡

መመሪያ

የክርስቶስ ተከታዮች ስለ ተግባራዊ ነገረ-መለኮት ወሳኝነት የመነጋገራቸው ነገር የተለመደ ጉዳይ ነው፡፡ ተግባራዊ ልናደርጋቸው የምንችላቸውን መልእክቶች መስማት በጣም እንፈልጋለን፡፡ እንዴት መኖር እንደሚገባን የሚስተምሩንን ትምህርቶች እንፈልጋለን፡፡ በዓለም ላይ በሚገኙ በርካታ ስፍራዎች፣ በሕይወታችን በእያንዳንዳቸው ጉዳዮች ላይ ተግባራዊ ልናደርጋቸው የምንችላቸውን መመሪያዎች የያዙ ጽሁፎች እናገኛለን፡፡ የያዕቆብ መጽሐፍ ግን ለዕለት ከዕለት ሕይወታችን ጥበብን በምንፈልግበት ወቅት የምንዘነጋቸውን ስነ-ልኮችና ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ነገሮችና ያሳየናል፡፡

የያዕቆብ መልእክት ለተግባራዊ አኗኗራችን ስለሚጠቅሙ በግልጽ ስለተቀመጡ በርካታ መመሪዎች የሚናገር መጽሐፍ ነው፡፡ እኛ ግን ሁለቱን ብቻ እንመለከታቸዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ያዕቆብ የእግዚአብሔርን ህግ እንዴት አድርጉ ከፍ አድርጎ

እንዳሳየው እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ ከእግዚአብሔር ህግ መካከል ያዕቆብ ቅድሚያ የሰጣቸውን እንመለከታለን፡፡ አስቀድመን የእግዚአብሔርን ህግጋት ስነ-ልክ እንመልከት፡፡

የእግዚአብሔር ህግ ስነ-ልክ

አብዛኞቹ የዘመናችን ክርስቲያኖች አዲስ ኪዳን ስለ ብሉይ ኪዳኑ የእግዚአብሔር ህግ የሚሰጣቸውን ማስጠንቀቂያዎች ያውቃሉ፡፡ አንዱን ብናነሳ፣ ድነት በጸጋ፣ በእምነት አማካይነት እንጂ በሥራ እንዳልሆነ እናውቃለን፡፡ በተጨማሪም ደግሞ በምንም ዓይት መንገድ ህግን በመፈጸም ድነትን ለማግኘት የሚደረገውን ጥረት የሚነቅፈውንና ወደ ገላትያ ሰዎች እና በሌሎች መልእክቶች ውስጥ የተገለጡትን የጳውሎስ መልእክቶችንም በትክክል እንከተላቸዋለን፡፡

በተጨማሪም፣ የእግዚአብሔርን ህግ በብሉይ ኪዳን ዘመን እንደሚኖር ሰው ተግባራዊ ማድረግ እንደማይገባንም እናውቃለን፡፡ እንደ ዕብራውያን የመሳሰሉ መጻሕፍት አጽንዖት የሰጧቸውን ጉዳዮች እና የእግዚአብሔርን ህግጋት ክርስቶስ፣ ሐዋርያት እና ነቢያት ባስተማሩን መንገድ በአዲስ ኪዳን ዘመን ተግባራዊ ማድረግንም በትክክል እናውቃለን፡፡

እንዚህ ማሳሰቢዎች እጅግ ወሳኝ መሆናቸው እሙን ቢሆንም፣ በያዕቆብ መልእክት ውስጥ ግን የምናገኛቸው ለየት ባለ መንገድ ነው፡፡ ያዕቆብ ስለ እግዚአብሔር ህግ የጠቀሰው እጅግ አዎንታዊ በሆነ አቀራረብ ነው፡፡ ለየት ያለ አጽንዖት የሰጠው በትውፊት "የህጉ ሦስተኛ ጥቅም" ተብሎ በሚጠራው ሃሳብ ላይ ነው፡፡ ሃሳቡም፣ ህጉን የምንፈጽመው እግዚአብሔር በክርስቶስ አማካይነት ለገለጠልን ምህረት ያለንን አድናቆት ለመግለጥ ነው፡፡ የሚለው ነው፡፡

ነፃ የሚያወጣው ህግ፡፡ ያዕቆብ በመልእክቱ ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ህግ ሁለት መግለጫዎችን ያቀርብልናል፡፡ ያም በእርሱ መልእክት ለየት ብሎ የቀረበ ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የሚነሳው፣ ነፃ የሚያወጣው ህግ የሚለውን ነው፡፡

ያዕቆብ ነፃ ስለሚወጣው ህግ የተናገረው በ1፡25 እና 2፡12 ውስጥ ነው፡፡ በዚያ ስፍራ የጠቀሰው ህጉ ከኃጢአት ባርነት እና ከዚያም የተነሳ ከሚመጣብን ጣጣ ነጻ ያወጣናል በማለት ነው፡፡ ህጉን ለእግዚአብሔር ካለን አድናቆት የተነሳ ከፈጸምነው፣ በእርግጥ ነጻ ያወጣናል፡፡ ይህንኑ ተመሳሳይ ሃሳብ ኢየሱስ በዮሐንስ 8፡32 ውስጥ እንዲህ ተናግሮታል፡፡

> **እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው (ዮሐንስ 8፡32)።**

ጳውሎስ በሮሜ 7፡7-13 ውስጥ፣ ህግ ኃጢአት እኛን የኃጢአት ባሪያዎች ሊደርገን ሲሻ በውስጣችን ክፉ መሻቶችን ለመቀስቀስ የሚጠቀምበት መሣሪያው ነው ብሎ ገልጾታል፡፡ ያዕቆብ ግን ህጉን የሚጠራው፣ "ነፃ የሚያወጣው ህግ" በማለት ሲሆን፣ መንፈስ ቅዱስ እኛን በተግባራዊ ጥበብ ሊያስታጥቀን ሲል አዎንታዊ በሆነ መንገድ ህጉ ባለሥልጣን መሪያችን እንዲሆን እንዴት እንደሚጠቀምበት ገልጾልናል፡፡

ቀደም ብለን እንዳየነው፣ ከያዕቆብ አንባቢዎች መካከል አብዛኞቹ ቤተክርስቲያንን በሚጎዱና እነርሱንም በተስፋ መቁረጥ ውስጥ በከተቷቸው ኃጢአቶች ተጠላልፈው ነበር፡፡ እናም፣ ስለ ጥበብ ያላቸውን የራሳቸውን አመለካከት መከተል ከቀጠሉ፣ ኃጢአት በሕይወታቸው ከሚያመጣቸው ተስፋ መቁረጦች፣ ችግሮችና ጉዳቶች ሊያመልጡ ፈጽሞ አይችሉም፡፡ ሆኖም አስቀድሞ የእግዚአብሔር ቃል ከኃጢአት ፍርድና ተገዢነት ነፃ እንዳወጣቸው ሁሉ፣ አሁንም በዕለት ከዕለት ሕይወታቸው ከሚገጥማቸው ብጥብጥና አመፅ ደግሞም በኃጢአት ምክንያት ከሚመጣባቸው ተስፋ መቁረጥ በቃሉ አማካይነት መንገዱን በማሳየት ነፃ ያወጣቸዋል፡፡

> **ህጉ በእርግጠኝነት መንገድ ያሳያል፣ ይገስጻል ደግሞም ያርማል አይደል? ያንንም የሚያደርገው የአማኞችን ሕይወት ለማቅናትና ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ወደተስማማ ሕይወት ለመመለስ ነው፡፡ እኔ እንደማስበው፣ ያዕቆብ በዚህ ስፍራ የሚያነሳው እኛም በስተመጨረሻ የሚፈረድብን በዚያው እርሱ ነፃ የሚወጣ ብሎ በጠራው በነፃነት ህግ አማካይነት እንደሆነ ነው፡፡ እኔም ያንን ነገር የምፈታው ነፃነቱ በክርስቶስ ያገኘነው ነፃነት ሲሆን፣ በዚህም ምክንያት እኛም ልንኖር ሚገባንና የእርስ በእርስ መስተጋብራችንንም ሊገዛ የሚገባው ይኸው እውነት ነው ብዬ ነው፡፡ እኛም የሚፈረድብን በዚው ህግ ሲሆን፣ በዚያም እግዚአብሔር ጸጋውን ያለ አድልዎ አፍስሶልናል፡፡**

እናም እኛ፣ ያንኑ ጸጋ፣ ለባለጠጋ ቢሆን ለድሃ፣ ለሸማግሌ ቢሆን ለወጣት፣ ለባሪያ ቢሆን ለነፃ ሰው፣ ለወንድ ሆነ ለሴት ልክ ሐዋርያ ጳውሎስ እንደተናገረው አንዳችን ለሌላችን ያለ አንዳች አድልዎ ልናካፍል ይገባናል፡፡

- **ዶ/ር ጄፊሪ ኤ. ጊብስ**

ያዕቆብ በ1፡22-25 ውስጥ በብርቱ እንዲህ ሲል የጠቀሰው ለዚህ ነው፡

> **ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ።**
> **ቃሉን የሚሰማ የማያደርገውም ቢኖር የተፈጥሮ ፊቱን በመስተዋት የሚያይን ሰው ይመስላል፤**
> **ራሱን አይቶ ይሄዳልና፥ ወዲያውም እንደ ምን እንደ ሆነ ይረሳል።**
> **ነገር ግን ነጻ የሚያወጣውን ፍጹሙን ሕግ ተመልክቶ የሚጸናበት፥ ሥራንም የሚሠራ እንጂ ሰምቶ የሚረሳ ያልሆነው፥ በሥራው የተባረከ ይሆናል (ያዕቆብ 1፡22-25)።**

ንጉሣዊ ህግ፡፡ የእግዚአብሔርን ህግ እንደ ነፃ አውጪ ህግ ከመግለጽ በተጨማሪ፣ የእግዚአብሔርን ህግ እንደ ንጉሣዊ ህግ አዎንታዊ በሆነ መንገድ ያዕቆብ ይገልጸዋል፡፡

ያዕቆብ ህጉን እንደ "ንጉሣዊ ህግ" የሚጠቅሰው በ2፡8 ውስጥ ነው፡፡ ይህ መግለጫ በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት አስመልክቶ የሚንጸባረቁትን አመለካከቶች እንድንቃኝ ያስገድደናል፡፡ የእግዚአብሔር ህግ የእርሱ "ንጉሣዊ ድንጋጌ" ነው፡፡ ከታላቁ ገዢ የመንግሥቱ ዜጎች ለሆኑ ህዝቡ የሚሰጥ ድንጋጌ ነው ማለት ነው፡፡

በእኛ ዘመን በምንኖረው ትውልዶች መካከል ግን የዚህን ንጉሣዊ ምስል ወሳኝነት በትክክል የመገንዘቡ ጉዳይ እጅግ ፈታኝ ይሆንብናል፡፡ እንዳንዶቻችን የምንኖረው ኃያል መንግሥታት በሚያስተዳድሯቸው አገሮች ውስጥ ነው፡፡ የያዕቆብ ተደራሲያን ይኖሩ የነበረው ግን በሮማው ንጉሥ ሥልጣን ስር ነበር፡፡ የእግዚአብሔርን ህግ "ንጉሣዊ ህግ" ብሎ መጥራት ለእነርሱ ምን ማለት እንደሆነ ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ በቀላሉ ስናስቀምጠው፣ የእግዚአብሔር ህግ እንዲሁ በቀላሉ የሚታይ ነገር እንዳልሆነ ይገባቸዋል፡፡ እኛ እንደፈለግን የምንወስደውና ካሻንም የምንተወው ነገር አይደለም ማለት ነው፡፡ የመጣው ከፍጥረተ-ዓለሙ መለኮታዊ ንጉሥ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት፣ የህጉ እያንዳንዱ ክፍል በእኛ ላይ የማይገሰስ ሥልጣን አለው ማለት ነው፡፡

ያዕቆብ በ2፡8-10 ስለ ንጉሣዊው ህግ ሥልጣን ሰፋ አድርጎ ከጠቀሰው ገሚሱን እንመልከት፡

> **..... የንጉሥን ሕግ ብትፈጽሙ መልካም ታደርጋላችሁ፤**
>
> **ለሰው ፊት ግን ብታደሉ ኃጢአትን ትሠራላችሁ፥ ሕግም እንደ ተላላፊዎች ይወቅሳችኋል።**
> **ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ፥ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል፤ ...**
> **(ያዕቆብ 2፡8-10)**

ከያዕቆብ ኤሁዳዊ ክርስቲያን ተደራሲያን መካከል አብዛኞቹ፣ ሁሉም ካልሆኑ ማለት ነው፣ የእግዚአብሔር ህግ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ያውቃሉ፡፡ በዚህ ስፍራ እንደምናየው ግን፣ ለህግዚአብሔር ህግ የሚገዙት እየመረጡ ነው፡፡ አንዳንዶቹን ይጠብቃሉ አንዳንዶቹን ደግሞ ቸል ይሏቸዋል፡፡ ስለዚህ፣ ህጉ "በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኝ ንጉሣዊ ህግ" እንደሆነ ያዕቆብ ያሳስባቸዋል፡፡ የተገኘውም ከመለኮታዊ ንጉሣቸው ነው፡፡ በዚህም ምክንያት፣ **"ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ፥ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል፤"**

ቀደምት የሆኑት ነገሥታት የሚያወጧቸውን ህግጋት ዜጎቻቸው እየመረጡ እንዲተገብሩ ማለትም ደስ ያላቸውን እየፈጸሙ ደስ ያላላቸውን ግን እንዳይፈጽሙ አይፈቅዱም ተቀባይነትም የለውም፡፡ በተመሳሳይም መንገድ፣ የክርስቶስ ተከታዮች

የእግዚአብሔርን ህግ ደስ ያላቸውን እየፈጸሙ ደስ የማይላቸውን ግን የማይፈጽሙ ከሆነ ይህ ደርጊት ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ቀደምት የሆኑት ሰብዓዊ ነገሥታት ይህንን የመሰለውን መርጦ የመፈጸም ድርጊት በንጉሣዊ ሥልጣኖቸው ላይ እንደ ማመጽ ይቆጥሩታል፡፡ እግዚአብሔርም ይህንን መሳዩን ድርጊት በእርሱ ንጉሣዊ ሥልጣን ላይ እንደማመጽ ይቆጥረዋል፡፡ የእግዚአብሔር ህግ የተግባራዊ ጥበብ ስነ-ልክ ነው፣ እናም ከልባቸው ለሚፈልጉትና ንጉሣዊ ድንጋጌዎቹን ለሚጠብቁ ሁሉ ነጻነትን ያስገኛል፡፡

ለተግባራዊ ጥበብ የሚያስፈልገው መመሪያ የሚገኘው ከእግዚአብሔር ህግ ስነ-ልክ ውስጥ እንደሆነ ያዕቆብ እንዴት እንዳመለከተ ዐይተናል፣ አሁን ደግሞ የእግዚአብሔር ህግ ቅድሚያ በሚሰጣቸው ጉዳዮች ላይ እንዴት ትኩረት እንዳደረገ ወደመመልከቱ እንሸጋገር፡፡

የእግዚአብሔር ህግ ቅድሚያዎች

እስኪ ፊት ለፊት እንጋፈጠው፣ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር የሰጠንን ትዕዛዛት ሁሉ ስለ መፈጸም ሲናገሩ፣ በቶሎ የምንሄደው ወደ ተግባራዊ ችግሮች ነው፡፡ ትዕዛዛቱ ግን ለማስታወስ እንኳን እስኪያዳግተን በርካቶች ናቸው፣ መፈጸሙማ ምን ያህ አናሳ እንደሚሆን ማሰብ ይቻላል፡፡ ስለዚህም፣ በጊዜ ከተገደበ ማንነታችን የተነሳ፣ በዚህኛው ወይም በዚያኛው ላይ ላማተኮር እንገደዳለን፡፡ እናም፣ በእርግጠኝነት፣ ሳንወድድ የእግዚአብሔርን ቃል ሥልጣን ወደ ማቃለሉ ወጥመድ ውስጥ እንገባለን፡፡ ያንንም የምናደርገው ልንታዘዛቸው ደስ በሚሉን ላይ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች በማተኮር መርጠን ማድረግ ስንጀምር ነው፡፡ ይህንን ችግር ለማስወገድ፣ ህጉ ራሱ ቅድሚያ እንድንሰጣቸው ያዘዘንን ለይተን ማወቅ ያስፈልገናል፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሔር ህግ ከፍተኛ ስፍራ በሰጣቸው እጅግ ወሳኝ ቅድሚያዎች ላይ ማትኮር ይገባናል፡፡

ኢየሱስ በማቴዎስ 22፡34-40 ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ህግ ቅድሚዎች እንደተናገረ ታስታውሳላችሁ፡፡ በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ፣ ሁለቱን ታላላቅ ትዕዛዛት ለይቶ ገልጾአቸዋል፡፡ የገለጻቸውም ምንም ሊያጠራጥሩ በማይችሉ ግልጽ ቃላት ሲሆን፣ ያም እግዚአብሔርን የመውደድ ትዕዛዝ ሲሆን፣ የተወሰደውም ከዘዳግም 6፡5 ነው፣ ያም በልቡናችን ልናኖረው የሚገባ ወሳኝ መርህ ነው፡፡ ከዘሌዋውያን 19፡18 ደግሞ፣ ባልንጀራን መውደድን ጠቅሷል፡፡ ያም ሁለተኛው እጅግ ወሳኝ መርህ ነው፡፡

እግዚአብሔርን መውደድ ከህግጋት ሁሉ የላቀው ህግ እንደሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ በትክክል ተረድቷል፡፡ በገላትያ 5፡14 ውስጥ ግን፣ ህግ ሁሉ ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ በተባለው ህግ እንደተጠቀለለም ተናግሯል፡፡ እጅግ ማራኪ በሆነ መንገድም፣ ያዕቆብም ያደረገው ያንኑ ነው፡፡ ያዕቆብ በሁለተኛው ታላቅ ትዕዛዝ ላይ ያደረገውን ለየት ያለ አጽንዖት በ2፡8-10 ላይ እንመልከት፡

> **ነገር ግን መጽሐፍ፡- ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ እንደሚል የንጉሥን ሕግ ብትፈጽሙ መልካም ታደርጋላችሁ፤**
> **ለሰው ፊት ግን ብታደሉ ኃጢአትን ትሠራላችሁ፥ ሕግም እንደ ተላላፊዎች ይወቅሳችኋል።**
> **ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ፥ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል፤**
> **አታመንዝር ያለው ደግሞ፡- አትግደል ብሎአልና፤ (ያዕቆብ 2፡8-10)**

ያዕቆብ በ19፡18 ውስጥ "ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ" በማለት የንጉሣዊውን ህግ ቅድሚያዎች እንዴት ጠቅለል አድርጎ እንዳስቀመጣቸው ልብ እንበል፡፡

ያዕቆብ ይህንን ያደረገበት ምክንያት ምሥጢር አይደለም፡፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ በባለጠጋና በድሃ አማኞች መካከል እየታየ ያለው ብጥብጥ የተከሰተው ይህንን ሁለተኛውን ታላቅ ትዕዛዝ ቸል ከማለታቸው የተነሳ ነው፡፡

ያዕቆብ በዚህ ስፍራ እንዳመለከተው ለባለጠጎች "አድልዎ የሚደርጉ ሰዎች" በራሱ በህጉ "እንደ ህግ ተላላፊዎች ይፈረድባቸዋል"፡፡ እናም ጉዳዩ ቀላል ጉዳይ አይደለም፡፡ ሌሎቹን ሁሉ እየጠበቀ ይህኛውን ብቻ የተላለፈ ሰው "ህጉን በጠቅላላ እንዳፈረሰ ሰው ይቆጠራል"፡፡ ስለዚህ፣ ለተግባራዊ ጥበብ ባለሙሉ ሥልጣን መመሪያ ሰጪ የሆነው

የእግዚአብሔር ህግ፣ እግዚአብሔርን በፍጹም ልባችን ከመውደድ በማስከተል ለእርስ በርስ መዋደዳችን ከፍተኛ ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ ያዕቆብ በ1፡27 ውስጥ ባለጠጎችን እንዲህ አሳስቧቸዋል፡

> **ንጹሕ የሆነ ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይህ ነው፤ ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ፥ በዓለምም ከሚገኝ እድፍ ሰውነቱን መጠበቅ ነው (ያዕቆብ 1፡27)።**
>
> **እንግዲህ፣ የእውነተኛ ሃይማኖት መፈተኛው ምንድን ነው? ግብረገባዊ የሆኑ ነገሮችን የማከናወን፣ በማኅበረሰቡ መካከል ገጽታህን የሚያሳምሩ ነገሮችን የማከናወን መፈተኛ ማለቴ አይደለም፣ እውነተኛ መፈተኛ ማለት የእግዚአብሔርን መንገዶች የመከተል ጉዳይ ማለት ነው፣ ማለትም እግዚአብሔር ወላጅ ስለሌላቸው ልጆች ግድ ይለዋል፤ እግዚአብሔር ስለ መበለቶች ግድ ይለዋል፡፡ ስለዚህ ምንም ምላሽ ሳትጠብቅ፣ ማንም አየኝ አላየኝ ብለህ ማድረግ፡፡ ለመሆኑ ወላጅ የሌለው ማን ነው? መበለትስ ማን ነው? ብንል ለእናንተ ብድር የማይመልሱ ሰዎች ናቸው፡፡ እንግዲህ፣ ለባልንጀራ ወይም ለአለቃህ መልካም ማድረግ የእውነተኛ ሃይማኖት ማረጋገጫ ሊሆን አይችልም፡፡ ግን፣ እንደምናውቀው፣ እግዚአብሔር ድሆችን ይወድዳል፤ እግዚአብሔር የደካሞች ደካማ ለሆኑት ይራራል ከእነርሱም አንዳች ቁሳዊ ምላሽን አይጠብቅም፡፡ እውነት ነው እርሱ ምሥጋናችንን ይቀበላል፣ እኛ በምናደርጋቸውም መልካም ነገሮች ደስ ይለዋል፡፡ ከሁሉ የሚልቀው መፈተኛ ግን፣ ብድር ለማይመልሱልን ሰዎች መልካም ማድረግ ነው፡፡**
>
> - **ዶ/ር ዳን ዶሪያኒ**

ባለጠጎች ድሃ የሆኑ ባልንጀሮቻቸውን በመውደድ የእግዚአብሔር ህግ ቅድሚያ የሚሰጠውን ነገር የመከተላቸው ነገር እጅግ አስፈላጊ ስለመሆኑ ያዕቆብ አጽንዖት ሰጥቶበታል፡፡ ባልንጀራን እንደ ራስ መውደድ ለተግባራዊ ጥበብ እጅግ ወሳኝ ስለመሆኑ የጠቀሰው ያዕቆብ ለድሆችም እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆንም አውስቷል፡፡ ጥቂት ምሳሌዎችን ለማንሳት ያህል፣ ያዕቆብ በመልእክቱ ከዳር እስከዳር ያነሳው ጉዳይ እንደሚያወሳው ባልንጀራን መውደድ ማለት አንደበትን ሌሎችን ለመባረክ ብቻ መጠቀምም እንደሆነ አሳይቷል፡፡

ያዕቆብ በ1፡19 ውስጥ "ስለዚህ፥ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ለቍጣም የዘገየ ይሁን፤" በማለት ጥሪ ያቀርባል፡፡ በ4፡1-3 ውስጥ ደግሞ ጦርነት፣ ብጥብጥ እና ሃሜት በእግዚአብሔር ህዝብ መካከል ሊገኝ እንደማይገባ ያዕቆብ ያሳስባል፡፡ በ4፡11 ውስጥ ደግሞ፣ "ሃሜትን" ረግሟል፡፡ በ5፡9 ውስጥ ደግሞ፣ "እርስ በርሳችሁ አትተማሙ" በማለት አዝዟል፡፡ ይልቁኑ በ5፡19 እንደምናየው፣ "እርስ በርሳቸው ኃጢአታቸውን እንዲናዘዙና አንዱ ስለሌላው እንዲጸልይ" ያበረታታል፡፡

በያዕቆብ ተደራሲያን መካከል ያሉ አማኞች ከሰማይ የሆነችውን ጥበብ ተቀብለናል የሚሉ ከሆነና ያንንም በተግባር ማሳየት ከፈለጉ፣ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ህግ ስነ-ልክ መስጠት ይገባቸዋል፡፡ ይህንንም ሊደርጉ የሚችሉት እርስ በርስ ባላቸው ፍቅር አማካይነት ለእግዚአብሔር ህግ ቅድሚያዎች እውቅና በመስጠት ነው፡፡

ያዕቆብ በተግባራዊ ጥበብ ላይ የሰጠው አጽንዖት የተደራሲያኑን ፍላጎት እና መመሪ እንዴት እንዳካተተው ስንመለከት ከቆየን፣ አሁን ደግሞ በሦስተኛ ደረጃ ወዳነሳው ጉዳይ ማለትም በእምነትና በተግባራዊ ጥበብ መካከል ስላለው ግንኙነት ወደመመልከቱ እንሸጋገር፡፡

እምነት

በክርስትና ውስጥ ማዕከላዊ ስፍራ ከሚይዙ ነገሮች መካከል አንዱ እምነት መሆኑ ነገር አያጠራጥርም፡፡ እኛ ሁላችን ክርስትና "እምነታችን" እንደሆነ እንናገራለን፡፡ የእምነታችን ማዕከልም (ዋና) ክርስቶስ እነደሆነ እንናገራለን፡፡ የፕሮቴስታንት አስተምህሮ የሆነውን ሶላ ፊደ ወይም ጽድቅ በእምነት ብቻ የሚለውንም እንቀበላለን፡፡ ዛሬ እውቅና የምንሰጠው የእምነት ወሳኝነት፣ በአዲስ ኪዳን በራሱ እምነት ማዕከላዊ እንደሆነ በተሰጠው አጽንዖት ላይ ነው፡፡ በመጀመሪያው ምዕተ-ዓመት

ክርስትናም ውስጥ እምነት ማዕከላዊ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ያዕቆብ ተግባራዊ ጥበብ ለተደራሲያኑ ያለውን ፋይዳ ለማሳየት ሲል የእምነትን ጉዳይ ያነሳል፡፡

ያዕቆብ ተግባራዊ ጥበብንና እምነትን ካገናኘባቸው መንገዶች መካከል በጊዜ ውስንነት ምክንያት ማንሳት የምንችለው ሁለቱን መንገዶች ብቻ ነው፡፡ በመጀመሪያ፣ ያዕቆብ በእምነትና በሥራ መካከል ያለውን ግንኙነት አብራርቷል፤ ሁለተኛ ደግሞ፣ ያዕቆብ በእምነትና በጽድቅ መካከል ስላለው ግንኙነት አብራርቷል፡፡ እስኪ አስቀድመን እምነትንና ሥራን እንዴት እንደዳሰሳቸው እንመልከት፡፡

እምነትና ሥራ

ያዕቆብ በ2፡14 ውስጥ ጉዳዩን የሚያነሳው ቀጥተኛ በሆነ ጥያቄ ነው፡

> **ወንድሞቼ ሆይ፥ እምነት አለኝ የሚል፥ ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን? (ያዕቆብ 2፡14)**

በእርግጥም፣ ያዕቆብ ላነሳው ጥያቄ ምላሹ፣ "በፍጹም" የሚል ነበር፡፡ በእምነት የማይረጋገጥና ራሱን በተግባር የማይገልጥ እምነት አያድንም፡፡

"እምነት" ወይም "ማመን" የሚለው ቃል *pistis* (πίστις) የሚለውን ስምና *pisteuō* (πιστεύω) የተሰኘውን ግስ የሚፈታ ቃል ነው፡፡ እነዚህ የቃላት ቤተሰቦች በአዲስ ኪዳን ውስጥ በመቶዎች ለሚቆጠሩ ጊዜያት ተጠቅሰው ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ቃላት በእንግሊዝኛው ቋንቋ እንደ "እምነት" እና "ማመን" ሁሉ የተለያዩ በርካታ ጽንሰ ሃሳቦችንም ያሳያሉ፡፡

ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፣ በአዲስ ኪዳን በአንድ ወቅት ውስጥ፣ እምነትና ማመን የአንድን ነገር እውነተኝነት ለማረጋገጥ በአዕምሮ እውቀት ከመስማማት ጋር ብቻ ይጣቀስ ነበር፡፡ በሆነ ወቅት ደግሞ፣ አንድን ጉዳይ ለተወሰነ ወቅት ተስማምቶ ከመቀበል ጋር ይጣቀስ ነበር፡፡ በሌላ ወቅት ደግሞ፣ የነገረ-መለኮት ምሁራን "የሚያድን እምነት" ብለው ከሚጠሩት ጋር ያጣቅሱት ነበር፡፡ የሚያድን እምነት በሙሉ ልብ፣ በሕይወት ዘመን ሁሉ ክርስቶስ ድነት መንገድ እንደሆነ ማመንና መደገፍ ማለት ነው፡፡ "እምነት" እና "ማመን" ማለት በርካታ ትርጉም እንዳለው ያዕቆብ እውቅና ይሰጣል፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ተደራሲያኑ አለን የሚሉትን እምነት እውነተኝነት እንዲፈትሹ ያዕቆብ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡ ለምሳሌ፣ በ2፡19 ውስጥ፣ አይሁድ ክርስቲያን ተደራሲያኑን ያዕቆብ እንዲህ በማለት ይሞግታቸዋል፡፡

> **እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል (ያዕቆብ 2፡19)።**

ያዕቆብ ተደራሲያኑ እንዳመኑ ሲቀበልና ሲስማማ፣ *pisteuō* (πιστεύω) ከተሰኘው ቃል ጋር አገናኝቶ ሲሆን ያዛመደውም አንድ አምላክ እንዳለ ከሚናገረውና *Shema* ከተሰኘው ቃል ጋር ነው፡፡ በዘዳግም 6፡4 የሚገኘውና "እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፤" የሚለው ይህ ጥንታዊ የብሉይ ኪዳን የእምነት አንቀጽ የሚነግረን ይህንኑ ነው፡፡ ከያዕቆብ አመለካከት አንጻር፣ ተደራሲያኑ ስለዚህ እውነት አዕምሯዊ ስምምነት ያላቸው የመሆኑ ነገር መልካም ነው፡፡ ሆኖም ግን መልካም የመሆኑን ያህል፣ ይህን መሳዩ እምነት ምንም እርባና የለውም ምክንያቱም፣ "አጋንንቶቹም ያንን ያምናሉና"፡፡ እንዲውም፣ አጋንንቱ ስለዚያ ሲያስቡ ይንቀጠቀጣሉ፡፡ ያ ግን ለእነርሱ ምንም አይረባም፡፡ መታዘዝ የሌለበት አዕምሯዊ ስምምነት ብቻውን የሚያድን እምነት አይደለም፡፡ ወይም ያዕቆብ በ2፡26 ውስት ቁርጥ አድርጎ እነዳስቀመጠው፡

> **ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው (ያዕቆብ 2፡26)።**

ስለ እምነትና ስለ ሥራ የተመለከትነውን ይህን ሃሳብ በልቡናችን ይዘን፣ ስለ እምነትና ስለ ጽድቅ ያዕቆብ ያነሳውንም እንመልከት፡፡

እምነትና ጽድቅ

የጻደቀ ማነው? ወይም በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ማን ነው? የሚለው ጥያቄ፣ በያዕቆብ ዘመን በነበሩ አስተማሪዎች መካከል ውዝግብ ያስነሳ ጉዳይ ነበር፡፡ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን በነበረችው ቤተክርስቲያን ውስጥም ጉዳዩ ማዕከላዊ ጉዳይ ሆኖ ዘልቋል፡፡ ጻድቅ ተብሎ የሚቆጠረው ማን ነው? ጻድቅስ ማን ነው? በ2፡21-24 ውስጥ ያዕቆብ ለዚህ ጥያቄ በዚህ መንገድ ምላሽ ይሰጣል፡

> **አባታችን አብርሃም ልጁን ይስሐቅን በመሠዊያው ባቀረበ ጊዜ በሥራ የጸደቀ አልነበረምን? እምነት ከሥራው ጋር አብሮ ያደርግ እንደ ነበረ፥ በሥራም እምነት እንደ ተፈጸመ ትመለከታለህን?**
> **መጽሐፍም፡- አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት ያለው ተፈጸመ፤ የእግዚአብሔርም ወዳጅ ተባለ።**
> **ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ (ያዕቆብ 2፡21-24)።**

በዚህ ስፍራ ያዕቆብ እየተናገረ ያለው ስለ መጽደቅ ሲሆን፣ የተጠቀመበትም የግሪክ ግስ *dikaioō* (δικαιόω)፣ ፍቺውም "ጻድቀሃል ብሎ ማወጅ"፣ "ማጽደቅ" ወይም "ነፃ ማውጣት/ማረጋገጥ" ማለት ነው፡፡ አብርሃም የጸደቀው ወይም ጻድቅነቱ የተረጋገጠው በሥራ ማለትም በዘፍጥረት 22 ተመዝግቦ እንደምናገኘው ልጁን ይስሐቅን ለእግዚአብሔር በመሰዋት ነው የሚል መከራከሪያ ያቀርባል፡፡ ይህንንም መሠረት በማድረግ፣ ማንም ሰው በእምት ብቻ ሊጸድቅ ወይም ጻድቅነቱ ሊረጋገጥ አይችልም ብሎ ይደመድማል፡፡ እግዚአብሔር ጻድቅ ነህ ብሎ የተቀበለው ማንኛውም ሰው መጽደቁ የሚረጋገጠው ከመጽደቁ የተነሳ በሚገለጠው ሥራ ነው፡፡

ያዕቆብ ያነሳው ይህ ሃሳብ ለበርካታ ዘመናት በርካታ ክርክሮችን ሲስነሳ ቆይቷል ምክንያቱም ሃሳቡ ጳውሎስ ስለ ጽድቅ ካነሳው ሃሳብ ጋር የሚቃረን ስለሚመስል ነው፡፡ በ2፡24 ውስጥ ያዕቆብ እንዲህ ይላል፡

> **ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ (ያዕቆብ 2፡24)።**

በተቃራኒው ደግሞ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ በገላትያ 2፡16 ውስጥ እንዲህ ጽፏል፡

> **ነገር ግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በሕግ ሥራ እንዳይሆን አውቀን.. (ገላትያ 2፡16)፥**

እንደ እውነቱ ከሆነ፣ በዚህ ስፍራ ምንም ተቃርኖ የለም፡፡ ይልቁኑ፣ ያዕቆብ እና ጳውሎስ የተጠቀሙት የግሪክ ቃል *dikaioō* (δικαιόω)፣ ወይም "መጽደቅ" የሚለውን ቃል ሲሆን፣ ያቀረቡት ግን በተለያየ መንገድ መሆኑ ነው፡፡ በጳውሎስ ነገረ-መለኮታዊ መዝገበ ቃላት መሠረት፣ መጽደቅ የሚለውን ቃል ቃል ለአንድ ነገር ብቻ ተጠብቆ እንዲቆይ አድርጎታል፡፡ ለጳውሎስ፣ ጽድቅ ማለት በክርስቶስ ኢየሱስ የጽድቅ ሥራ አማካይነት በክርስቶስ የመዳን እምነት የተቀበሉ ሁሉ ጸድቃችኋል ተብለወ የታወጀበት የመጀመሪያ አዋጅ ማለት ነው፡፡

ሆኖም፣ ያዕቆብ፣ ስለ ጽድቅ የሚናገረው ለየት ባለ መንገድ ነው፡፡ ያዕቆብ *dikaioō* (δικαιόω)፣ የሚለውን ቃል ሲጠቀም አጠቃቀሙ፣ "መጽደቅን ማረጋገጥ" ወይም "ጽድቅን ማረጋገጥ" የሚለውን የሚሳይ ነው፡፡ አንድ ሰው ለመዳን የሚያበቃውን እምነት ለመቀበል ከሁሉ አስቀድሞ በክርስቶስ የተገኘውን ጽድቅ የመቀበሉን ጉዳይ በፍጹም አልካደም፡፡ ለያዕቆብ፣ *dikaioō* የተሰኘው ቃል ተግባራዊ የሚሆነው በጌታ በኢየሱስ ማመኑን የተናገረ ሰው መንፈስ ቅዱስ በሕይወቱ በሚሠራው ሥራ "መጽደቁ ይረጋገጣል" ወይም "ጽድቁ ይገለጣል" በሚለው እውነት ነው፡፡ ከያዕቆብ አመለካከት አንፃር፣ የመንፈስ ቅዱስ የማስቻል ኃይል አንድን ሰው ለክርስቶስ የተሰጠ እንዲሆን ያስችለዋል፡፡ አንድ ሰው ስለ አማኝነቱ በየትኛውም ውብ ቃል ሊያውጅ ቢችልም፣ እምነቱን በመልካም ሥራ እስካልገለጠው ድረስ፣

በመጨረሻው አማኝነቱ ሊረጋገጥ አይችልም፡፡ ስለዚህ፣ ያዕቆብ በእምነትና በጽድቅ መካከል ስላለው ግንኙነት ሲያወሳ መናገር የፈለገው የተግባራዊ ጥበብን ወሳኝት ለአንባቢያኑ ለማስረዳት አስቦ ነው፡፡

> **በጳውሎስ እና በያዕቆብ መካከል ያለ የሚመስለን ግጭት ዋነኛ መንስዔው ጽድቅ በእምነት ብቻ የተሰኘው ሃሳብ ሲሆን፣ እኔ እንደማስበውም ይህ ጎላው በያዕቆብ መጽሐፍ ውስጥ ነው፡፡ ምናልባትም እኔ እንደምረዳው፣ በመጽሐፉ ውስጥ ከተጠቀሱ ከሌሎች ጉዳዮች ይልቅ ይህኛው ጉዳይ ብዙ ትኩረት የተሰጠው ይመስለኛል (በእንግሊዝኛ ተናጋሪዎቹ ዘይቤያዊ አገላለጽ ብዙ ቀለም የፈሰሰበት የተሰኘው ለማለት ነው)፡፡ ከሁሉ አስቀድሜ ልናገር የምፈልገው፣ *dikaioō* የተሰኘው የግሪኩ ቃል አንዳንድ ጊዜ "የጽድቅ ሥራ" ተብሎ ይፈታል፣ ማልም እኔ በቻልኩት መጠን አሳጥሬ ላቀርበው ብሞክር፣ ጽድቅ በመሠረቱየአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ዓይነት ነው፡፡ በአንድ በኩል፣ ይቅርታን አግኝተናል፣ ማትም እግዚአብሔር ይቅር ብሎናል፡፡ ያኛው ከእኛ ዕዳን የመውሰዱ ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ ጎኑ ደግሞ የተጨመረልን ነገር አለ፣ ያም ጽድቅን መቀበላችን ነው፡፡ ያም እንግዲህ "በእኔ ፊት እናንተ የምትታዩት ጻድቃችሁ ነው" የሚለውን አዋጅ ይይዛል ማለት ነው፡፡ እናም፣ እኛ ጻድቀናል፣ ያ ማለት አንደኛው ጽድቅ የተሰኘው ቃል አንዱ ፍቺ ይህ ነው ማለት ነው፡፡ በሌላ ጎኑ ደግሞ፣ ጽድቅ የሚለውን ቃል "ማረጋገጥ" ወይም "መጽደቅን ማሳየት" ብለን ልንፈታው እንችላለን፡፡ ስለዚህ ጳውሎስ ቃሉን የተጠቀመው ከህግ ጋር ተያያዥነት ባለው የህክምና ማስረጃ አቀራረብ (Forensic) መንገድ ሲሆን፣ ያዕቆብ የተጠቀመበት ደግሞ መጽደቅህን ሌሎች ሁሉ ሊያዩ በሚችሉበት መንገድ ከምታረጋግጥበት የጸደቀ ሰው ሥራ ጋር ነው፡፡ ስለዚህ፣ ስናጠቃልለው፣ ጳውሎስ ጽድቅ የተሰኘውን ቃል ሲጠቀም ያመለከተው የእምነትን ቀዳሚነት ሲሆን፣ ያዕቆብ ደግሞ ጽድቅ የሚለውን ቃል የተጠቀመበት ከድነት-በኋላ አማኝነት የሚረጋገጥበትን ሕይወት ለማሳየት ነው፡፡ ስለዚህ የያዕቆብ ጥያቄ "ጻድቅ ተብሎ ሊነገርለት የሚችል ማን ነው? በእግዚአብሔር አምናለሁ እያለ የሚናገር ወይስ በእግዚአብሔር አምናለሁ ብሎ ያወጀውን እምነቱን በሚያረጋግጥ መንገድ እየኖረ የሚያሳይ ነው?" የሚል ነው፡፡ ስለዚህ ለጳውሎስም ሆነ ለያዕቆብ እምነት ማለት ራሱን ተግባር የሚገልጥ ነው ማለት ነው፡፡ ደግሜ ልናገረው፣ እምነት ራሱን በተግባር የሚገልጥ ነው፡፡ በግልጽ የሚታይ ሊሆን ይገባል፡፡ በቃላት ማነብነብ ብቻ አይበቃም፡፡ አዕምሮአዊ እውቀት ብቻውንም በቂ አይደለም፡፡ እምነት ወደ ተግባራዊ እርምጃ መዝለቅ አለበት፡፡ በመከራ ይጸናል፣ የእግዚአብሔርን ቃል ይፈጽማል፣ በተግባር የሚገለጡ ሰዎችን ያበዛል፣ ቂም አይቋጥርም፣ አንደበትን ይገራል፣ በጥበብ ይገለጣል፣ የጌታንም ዳግመኛ መመለስ በትዕግሥት ይጠባበቃል፡፡ እናም ጳውሎስና ያዕቆብ ያስተማሩት ፍጹም አንድ የሆነ እውነት ነው፡፡**
>
> **- ዶ/ር ላሪ ጄ. ዋተርስ**

ያዕቆብ ይህንን መርህ በተግባር የገለጠበትን የ2፡15-17 አገላለጽ እናድምጥ፡

> **ወንድም ወይም እኅት ራቁታቸውን ቢሆኑ የዕለት ምግብንም ቢያጡ፥**
> **ከእናንተ አንዱም፦ በደኅና ሂዱ፥ እሳት ሙቁ፥ ጥገቡም ቢላቸው ለሰውነት ግን የሚያስፈልጉትን ባትሰጡአቸው ምን ይጠቅማቸዋል?**
> **እንደዚሁም ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው (ያዕቆብ 2፡15-17) ።**

ያዕቆብ ከዚህ በላይ ነጥቡን በብርቱ ሊገልጥ የሚችልበት መንገደ ሊኖር ይችላል ብሎ ማሰብ ይከብዳል፡፡ ተደራሲያኑ በቤተክርስቲያናቸው ውስጥ ለተነሳው ብጥብጥ ምላሽ ሊሰጡ የሚገባው ለእግዚአብሔር ትዕዛዝ ተግባራዊ ምላሽ በመስጠት ነው፡፤ ማለትም፣ እርስ በርስ እንዲዋደዱ የሰጠውን ትዕዛዝ ማለት ነው፡፡ ስለ እምነታቸው የትኛውንም የአንደበት አዋጅ ሊያውጁ ይችላሉ፣ ነገር ግን አማኝነታቸውን ሊታይ በሚችል የፍቅር ተግባር እንዲታይ ካላደረጉት በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን መሆናቸው ሊረጋገጥ አይችልም፡፡

ማጠቃለያ

በዚህ ትምህርት በያዕቆብ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን ሁለቱን የጥበብ መንገዶች ተመልክተናል፡፡ ማሳሰቢያ ሰጪ ጥበብ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን በማሳየት ስለ ማሳሰቢያ ሰጪ ጥበብ ለተደራሲያኑ መልእክት ያስተላለፈ መሆኑን፣ መመሪያም የሰጣቸው መሆኑን፣ በእምነትና በማሳሰቢያ ሰጪ ጥበብ መካከል ስላለውም ግንኙነት ያወሳላቸወ መሆኑን አይተናል፡፡ ለእግዚአብሔርና ለህዝቡ የታመነ አገልግሎት በማቅረብ የእግዚአብሔርን ቃል በተግባር ማሳየት የሚችሉበትን መመሪያ በማቅረብና ማሳሰቢያ ሰጪ ጥበብ የሚያስፈልጋቸወ መሆኑን በማመልከት እንዴት ማሳሰቢያ ሰጪ ጥበብን ሊናፍቁና በብርቱ ሊፈልጉ እንደሚገባቸው እንዳመለከተም አስተውለናል፡፡

የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ክርስቲያኖች ሁለቱን የጥበብ መንገዶች እንዲከተሉ ያዕቆብ ጥሪ ያቀርባል፡፡ ዛሬም ለእኔና ለእናንተ ያው እውነት ያስፈልገናል፡፡ እኛም መመሪያ ሰጪም ተግባራዊ ጥበብም ሁለቱም ያስፈልጉናል፡፡ እነዚህን ስጦታዎች ከእግዚአብሔር ለመቀበል፣ ያዕቆብ ለሰጣቸው መመሪያዎች ራሳችንን ማስገዛት ያስፈልገናል፡፡ ያንንም ለእግዚአብሔር ባለን ጽኑ እምነትና መሰጠት ልናረጋግጠው ይገባል፡፡ ምድራዊውን ጥበብ መከተል የሚቀለን ሆኖ ራሳችንን ካገኘነው፣ የያዕቆብን መጽሐፍ ብድግ አድርገን ከእግዚአብሔር የምትገኘውን ጥበብ ወደ ልባችን ማስገባትና መንገዷንም መከተል ምርጫችን ማድረግ ይገባናል፡፡